# ሥርዓተጾታ በጻራ ማኅበረሰብ ባህል

**ፍሬህይወት ባዩ**[1]


**አጽህሮተ ጽሁፍ**

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት፣በካፋ ዞን ከሚገኙ ብሄረሰቦች መካከል አንዱ በሆነው የጻራ ማህበረሰብ ዘንድ የሥርዓተ ጾታን ምንነት፣ ዓይነትና አንድምታ በፎክሎር የጥናት ማእቀፍ መመርመርነው።የጥናቱ ዓላማ ሴቶች በተጠቀሰው ማኅበረሰብ ምን ዓይነት ማህበራዊ ቦታ/ሚና እንዳላቸው፣ ምን ዓይነት ማኅበራዊ ሃላፊነት እንደሚጠበቅባቸውና እንደሚሰጣቸው፤በሀገረሰባዊ እምነት ውስጥ እንዴት እንደተሳሉ፣ በልማዱ ምን ማድረግ እንደሚፈቀድላቸው እና/ወይም እንደማይፈቀድላቸው፣ በመመርመር ማኅበረሰቡ ለሴቶች ያለውን አመለካከትና በጥቅሉ ለሴትነት ያለውን አስተሳሰብ ማሳየት ነው። ስለሆነም ጥናቱ የጻራን ብሄረሰብ ማንነት፣ አስተሳሰብና አመለካከት በጥልቀት ለመረዳት ከፍ ያለ ፋይዳ ይኖረዋል። በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋና ጉዳይ ሥርዓተ ጾታን፣ ምንነት ትርጉም ምን እንደሆኑ በይበልጥ ከመስክ የተገኘ መረጃን ከፎክሎር እይታ አንፃር በመተንተንና በመተርጎም ማሳየት ነው። የምርምር ማእቀፉየአይነት/ የትርጉም (Qualitative/ interpretative) ነው። በጥናቱ አካባቢ ከተመረጡ የመረጃ አቀባዮች በቃለመጠይቅ እንዲሁም በምልከታና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት የተገኘ ቀዳማይ መረጃ ነው። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው አንዲት ሴት ከመወለዷ እስከ ሞቷ በመቃብር ሆና የሙት መንፈሷ ጭምር ከወንድ የተለየ መገለጫዎች አሉት። መገለጫዎቹ ማህበረሰቡ ሴትነትን የሚያይበት የእምነት/ የባህል እሳቤ ነው። እናት ስትወልድ ልጇ ሴት ከሆነች እትብቷ በሴት ወግ ይቀበራል። ህጻንነቷ በሴት ወግ ይቃኛል። ልጅነቷ በሴት ወግ ይገራል። ጋብቻዋ በሴት ደንብ ይፈጸማል። በጠቅላላው ኑሮዋ በሴትነት እሳቤ ይመራል።ትውፊታዊ መሠረት ያላቸው የጾታ ሚናን የሚመለከቱ ልማዶችም ከማህበረሰቡ ዘንድ መገለልን ስለሚያስከትሉ ልዩነቱን አሜን ብሎ ለመቀበል የግድ ይላሉ።


**ቁልፍ ቃላት፡- ሥርዓተ ጾታ፣ ሴትነት፣ ባህል፣ ሀገረሰባ እምነት**

## 1. መግቢያ

የሥርዓተ ጾታ (gender) ጉዳይ በኢትዮጵያ በተለይ ከ1990ዎቹ ወዲህ በተመራማሪዎች ዘንድ ትኩረት እያገኘ የመጣ ክስተት በመሆኑ፣ በዛ ያሉ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የባህልና የሥነ ጽሑፍ ተመራማሪዎች ጭብጡን ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች አንጻር ለማሳየት ሞክረዋል። እንደ አራጌ (2001) እና Selamawit (2006) ያሉ አጥኚዎች ጾታና ሥርዓተ ጾታን ከሃይማኖት ጽሑፎች አንጻር ለማየት

[1]ፒኤችዲ፣በአዲስ አበበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የባህል ተመራማሪ፡ firebayu@gmail.com/firehiwot.bayu@aau.edu.et

ሲሞክሩ፣ እንደ አዲሱ (2000)፣የሺዋስ(2007) ያሉት ተመራማሪዎች ደግሞ ሴትና የሴትነት ጽንሰ ሐሳብን ከሥነ ጽሑፍ ሥራዎች አኳያ ለመመርመር ጥረዋል። Tsion (2007 እ.አ.አ.)፣ Kalkidan (2007)፣ Yilma (2009)፣ Jejaw (2011)፣ Jemila (2014)፣ አዳነች(2002)፣ ለማ(1999) እና አልሳቤጥ(2005) ያሉት ምሁራን ደግሞ ርእሰ ጉዳዩን ከአንድ ብሔረሰብ/ማኅበረሰብ አንጻር ለመመርመር ሞክረዋል።

እነዚህ ጥናቶች በሥርዓተ ጾታ ላይ የሚደረገው ጥናት በየዘመኑ የተመራማሪዎችን ትኩረት ምን ያህል መሳብ እንደቻለ ማሳያ ናቸው። በሴትና በሴትነት ወይም በጾታና በሥርዓተ ጾታ ላይ የሚደረገው ጥናት ባንድም ይሁን በሌላ መንገድ ማኅበረሰቡን በሚገባ ለማወቅ የሚደረገውን ጥረት ማገዙ ስለማይቀር የዚህ ዓይነቱ ጥናት ጠቀሜታው ብዙ እንደሆነ ይሰማኛል። ለዚህም ነው በጻራ ማኅበረሰብ ላይ በማተኮር የሥርዓተ ጾታን ምንነት፣ ዓይነትና አንድምታ ለመመርመር የተነሳሁት። ጥናቱ የብሔረሰቡን ማንነት፣ አስተሳሰብና አመለካከት በጥልቀት ለመረዳት ከፍ ያለ ፋይዳ ይኖረዋል። የጥናቱ ዓላማ ሴቶች በጻራ ማኅበረሰብ ውስጥ ማህበራዊ ቦታ እና ሚናበተግባር የሚገለጽባቸውን ባህላዊ ድርጊቶች ለይቶ አንድምታቸውን ማሳየት ነው።ዝርዝር አላማውም አንደኛ፤በጻራ ማኅበረሰብ ሥርዓተ ጾታ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ የሚገለጥባቸውን መልኮች ለይቶ መተንተን። ሁለተኛ፤ በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ያሉትን የሥርዓተጾታ ማሳያዎችን ለይቶ መተንተን ሲሆን ሶስተኛው በባህሉ ነውር የተባሉ እሳቤዎች የሚገለጡበትን የሥርዓተጾታ ማሳያ በመመርመር ማኅበረሰቡለሴቶች ያለውን አመለካከትና በጥቅሉ ለሴትነት ያለውን አስተሳሰብ ማሳየት ነው። እግረ መንገድም የወንዶችን ሚና ይዳስሳል።

በእርግጥ እንደጻራ ባሉ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች ዙሪያ የተደረጉና በመደረግ ላይ ያሉ ምርምሮች በዓይነትም ሆነ በብዛት ውስን ናቸው። ውስን የሆኑትም ቢሆኑ አንዳንዶቹ በጻራና በአካባቢው አጎራባች ሕዝቦች ላይ ተመርኩዘው አጠቃላይ ዳሰሳ የሚያደርጉ (ለምሳሌ Lang፣ 1975) ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ስለጻራ ሁለንተናዊ ገጽታ ሁሉን አቀፍ መረጃ የሚሰጡ (ለምሳሌ Addisalem and Abera 2013) ናቸው። በማኅበረሰቡ አንድ ነጠላ ጉዳይ በተለይም በሥርአተ ጾታላይ ያተኮረ ጥናት መኖሩን የሚያሳይ መረጃ አላገኘሁም። ይህ ጥናት ትኩረቱን ሰብስቦ፣ አድማሱን አጥብቦ በጻራ ማኅበረሰብ ሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች ላይ በዋናነት የሚያጠነጥን በመሆኑ ከላይኞቹ ጥናቶች ይለያል።

ስለሆነም ይህ ጥናት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባህል ላይ ለሚደረጉ ጥልቅ ጥናቶች የራሱን በጎ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለኝ። እንዲህ ያሉ ትኩረታቸውን በአንድ ነጠላ ጉዳይ ላይ ያደረጉ ጥናቶች ስለ ኅብረተሰቡ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ያኗኗር ፍልስፍና የሚያንጸባርቁት ጉዳይ መኖሩን የሚያሳዩ ናቸው። በዚህ ጥናት የሚቀርበው ግኝት ተጨማሪ ማረጋገጫ ስለሚሆን በሌሎች መስኮችም ተመሳሳይ ጥናት እንዲካሄድ፤ በግኝቶቹና በጭብጦቹም ላይ ውይይት እንዲካሄድ ያበረታታል። እንዲህ ዓይነት ጥናቶች የኅብረተሰብ ተሃድሶን ለማምጣት የፖሊሲ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉበት ዕድል ሊኖር ስለሚችል ፋይዳቸው ከፍ ያለ ነው።

ጻራ('ጫራ'[2])የብሄረሰቡ መጠሪያ ነው::ልዩ ልዩ ጽሁፎች "ጫ"ን በ"ጸ" ምትክ በመጠቀም "ጫራ(Chara)" ብለው ይጠሯቸዋል:: በተለያዩ ጽሁፎችም በዞኑ ውስጥ በሚጻፉ ደብዳቤዎችና መሰል ሰነዶች ጭምር"ጫራ" የሚለውን ይጠቀማሉ::ጻረሳ ደግሞ ከኦሞቲክ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደበው የቋንቋቸው መጠሪያ ስም ነው:: ጻራ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በካፋ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ብሄረሰቦች አንዱ ነው:: በዞኑ ከሚገኙ አስራአንድ ወረዳዎች አንዱ በሆነው እና 22 ቀበሌ በያዘው ጎባ ወረዳ ይኖራሉ:: አጠቃላይ የህዝቡ ብዛት በ1998ዓ.ም የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሠረትጠቅላላው የጻራ ህዝብ ብዛት13,214 ሲሆን፤ ሴቶች6,638 ፣ 6,541ወንዶች እንደሆነ ይገልጻል(ገጽ 72):: ጻራ በሰሜን የካፊቾ ብሄረሰብ፣ በሰሜናዊ ምእራብ የናኦ ብሄረሰብ፣ በሰሜን የኮንታ ልዩ ወረዳ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ እና በደቡብ እንዲሁም በደቡብ ምእራብየመኤኔት ብሄረሰብ ያዋስኑታል(የብሄረሰቦች ምክር ቤት ፕሮፋይል፣ 2002):: ዋነኛ የስራ መስክ እና መተዳደሪያቸው ከብት እርባታ፣ እርሻ ስራ እንዲሁም ንብ ማነብ ናቸው::

ጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለሲሆን የጥናቱ ማእቀፍ ፎክሎር ነው:: በፎክሎር መስክ ለጥናት ዋና የመረጃ ምንጭ የባህሉን ባለቤቶች ባሉበት በመገኘት መረጃ ማግኘት መቻል ነው::ከጥር 2009 እስከ ሰኔ 2013ዓ.ም.ድረስ በተለያየ ጊዜ ማህበረሰቡ በሚኖርበት ካፋ ዞን ጎባ ወረዳ ዮካ፣ ሽዳ፣ ሻሽገበራ፣ ኦገያ፣ ዲሺ፣ ገሳ እና አንገላ ቀበሌዎች በመገኘት አስራ ስድስት (ስምንት ሴት እና ስምንት ወንዶች) በቃለመጠይቅ መረጃ ሰጥተዋል:: ሁለት የትውፊታዊ እምነት ክዋኔ ላይ አጥኚዋ በአካል በመገኘትበምልከታ መረጃ ተሰብስቧል:: መረጃው ሲሰበሰብ የተሻለ አሻሚ ሀሰቦችን ማጣራት ባስፈለገበት ጊዜ እያንዳንዱ ስድስት ስድስት አባላት ያሉት ሁለት የቡድን ውይይት ተደርጓል::በዚህ የቡድን ውይይት ላይ በቃለመጠይቅ ባህላዊ ክዋኔው ስለመደረጉ እንጂ ለምን እንደሚደረግ ምላሽ ባልተገኘባቸው መረጃዎች ላይ ውይይት ተደርጓል:: በጥናቱ ትንተና ውስጥ የተጠኚውን ማህበረሰብእውቀት መሠረት እንዲያደርግ ጽንሰ ሀሳቦችን የተሸከሙ የጻረሳ ቃላት እንዳለ በመጠቀም እና የያዙትን ጽንሰ ሀሳብ ትርጉም በመስጠት መረጃዎቹ ተተንትነዋል::

ጾታ (sex) የሴትና የወንድ ተፈጥሯዊ የጾታ ድልድልን የሚያሳይ ሲሆን፣በባህሪዪው ሁለንተናዊ በመሆኑ በጊዜና በቦታ ሊለወጥ አይችልም::[3]እያንዳንዱ ባህል ለጾታ ልዩነቶች (ሴት ስለመሆን እና ወንድ ስለመሆን)የዳበሩ አተያዮችና እና ልምዶች አሉት:: ሥርዓተ ጾታ (gender) ተፈጥሯዊ ከሆነው "ሴት" አልፎ ማኅበራዊና

---

[2]"ጻራ" የሚለው ህዝቡ እራሱን የሚጠራበት ቃል ነው:: መረጃው የተገኘው ለዚህ ጥናት በአካል መስክ በመገኘት በቃለመጠቅ እና በቡድን ውይይት ነው:: በተጨማሪም Lang, 1975ዓ.ም. ለህትመት ባበቃው ጥናቱ ይሄንኑ አረጋግጧል:: ሆኖም ክልሉን፣ የሚኖሩበትን ዞንና ወረዳ ጨምሮ የህዝቡን መጠሪያ ጫራ ይሉታል:: በዚህ ጥናት ጻራ የሚለውን እጠቀማለሁ:: ምክንያቱም ባለቤት የሆነው ህዝብ 'ስሜ ይሄ ነው' ያለውን መከተሉ አግባብነት ስላለው ነው::

[3] በአሁኑ ዘመን የቴክኖሎጂና የሳይንስ እድገት ውጤት በሆነው በቀዶ ህክምና የሚደረገውን የጾታ ሽግግር (transgender/transsexism) እውነታ ለጊዜውም ቢሆን ግምት ውስጥ ሳላስገባ ማለቴ ነው:: የጾታ ሽግግር ተፈጥሯዊ የሆነውን የመጀመሪያ ጾታ በመተው በህክምና እርዳታ ወደሌላ ጾታ የሚደረግን ለውጥ የሚመለከት ሐሳብ ነው::

ባህላዊ የሴት ውክልና፣ ውክልናው የቆመለትን ሐሳብ፣ ሐሳቡ የሚያመላክተውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የሃይል ትስስር (power relation) የሚያሳይ ነው። የሥርዓተ-ጾታ ሚናዎች ምንጭ በሴቶች እና በወንዶች መካከል ካሉ እና ከሚታወቁ ማህበራዊ ደረጃ እና ልዩነቶች የሚመነጩ ናቸው። የሥርዓተ-ጾታ ሚናውም የሚወሰነው በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መሠረት በሆኑ ደንቦች እና እሴቶች ነው(Leach 2004)። በሌላ አነጋገር፣ ሥርዓተ ጾታ ባህላዊና ማኅበራዊ ስራት በመሆኑ የሰዎችን አስተሳሰብና አተያይ፣ አመለካከትና አተረጓጎም በአሉታዊም ሆነ በአዎንታ ይቀይራል።ይህም ሲባል ጾታ ለሥርዓተ ጾታዊው እይታ በመነሻነት ያገለግላል።

ከተወለድን ጀምሮ እስከሞታችን የጾታ ግንኙነት መፈጠር የሕይወታችን ቋሚ አካል ነው። በሥርዓተጾታ ፅንሰሀሳብ፣ የጾታ ማንነታችን ለመቅረጽ በመጀመሪያዎቹ አመታት በተለይምእኛ ማህበራዊውን ዓለም በምን መለከተበት እና ሌሎች እኛን የሚመለከቱበት እይታ ወሳኝ ነው። በእርግጥ የሥርዓተ-ጾታ ግንባታ ከቦታ ቦታ ወይም ከባህል ባህል ይለያያል። እንዲሁም በአንድ ቦታ ወይም በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥያለው በራሱ በጊዜሂደት ይለወጣል(Leach 2004; Disch 1996)። ይህም ሥርዓተ ጾታ ስራቱ የባህል አካል መሆኑን ማሳያነው።

ባህል ደግሞ በማህበራዊ ደረጃ በወንዶች እና በሴቶች የተገነባ እና ተለዋዋጭ ሂደት ነው።ስለዚህ ሥርዓተጾታ በተለያዩ ባህሎች እና ታሪካዊ ክስተቶች አውድ ውስጥ ያልፋል (Hirut 2002)። ሂደቱም በሥርዓተ ጾታው ግንባታ እና የተገነባበትን አተያይ የተለያዩ ማህበረ ባህላዊ ለውጦች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ይለውጡታል። ስለዚህ የሥርዓተጾታ ጉዳይ በአንድባህል እና ማህበረሰብ ውስጥ እንኳን ቋሚ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው።

ሥርዓተጾታ የባህላዊ እሴቶች መገለጫ ነው። በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ጋብቻ አንዱ አካል ነው።በአንድ ወንድ እና ሴት መካከል የሚፈጸም ጋብቻ የጥንዶቹ ብቻ ሳይሆን የሚኖሩበት ማህበረሰብ ማሳያም ነው።በተለይም የጋብቻ ሂደቱ የሚመራበት የባህል አተያይ የሥርዓተ ጾታው ማሳያ ነው።ለምሳሌ በአፍሪካ ላይ የተጠናው ጥናት፤በአብዛኞቹ የአፍሪካ ማህበረሰቦች ልማድየሴት ልጁን የወደፊት ባል የመምረጥ መብት ያለው አባት(ወንድ) ነው። አንድ ባል ለመሆን የፈለገ ወንድ፣ የፈለጋትን ልጅ ለማግባትከአባቷ ፈቃድ ባለፈሀብት ካለውየመረጣትን ሴት ያገባል። ሴት ልጅ የወላጆቿን በተለይም የአባቷን ፍላጎት የማትከተል ከሆነ ከቤተሰቧም ሆነ ከማህበረሰቡ የተለያየ ተጽእኖ ይደርስባታል። ከዚህ ባለፈም ወጣት ሴቶች በለጋ እድሜያቸው ብዙ ሚስቶች ካሉት አዛውንት ጋር እንዲጋቡ ይገደዳሉ (Hunter 1995)። ይህ የሚያሳየን የማህበራዊ ግንኙነቱ መሰረት የሥርዓተ ጾታ ጉዳይም እንዳለበት በዚህም የሴቶችን እና የወንዶችን ሚና ጭምር የሚወስን መሆኑንነው። ሌላው በባህል ውስጥ ያለውየሥርዓተ ጾታ መገለጫ የሆነው ማህበራዊ ሚና የስራ ድርሻ ነው። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ብቻ ያለው የስራ ክፍፍል የሥርዓተ ጾታ ማሳያ ነው። በዚህ መስክ ከተጠኑ ጥናቶቶች አንዱ፤ አብዛኞቹ ሴቶች "ልጅማሳደግ

የቤት ውስጥ ተግባራትን እንደ ምግብ ማዘጋጀት፣ ቤት ማጽዳት፣ ውሃ መቅዳት፣ ማገዶ መሰብሰብ፣ ማለብ እና መጠለያን መጠበቅ የሴቶች 'ልዩ ኃላፊነት' እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ (Indra 2005)። በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ልምድ እንዳለ "ኢትዮጵያውያን ሴቶች እንደ እናት፣ ሚስት፣ የቤት ሰራተኛ ሆነው ከማገልገላቸውም በላይ የዚህ ባህል ባለቤት እና አስቀጣይ በመሆን ረገድም ሚናቸው የላቀ ነው"(Alem 2007) ሲሉ ይጠቁማሉ።

የሥርዓተጾታ ሌላው መገለጫ ነውር(ታቡ) ነው። የሚደረጉ እና የማይደረጉ ተብለው በየማህበረሰቡ የተለመዱ ክዋኔዎች እና ደንቦች አሉ። ለምሳሌ ምግብ እናየአመጋገብ ልማዱአንዱ ማሳያ ነው። "እንደየማህበረሰቡ የምግብ አዘገጃጀት እና የአመጋገብ ልማድ የተለያየ ነው። ልዩነቱም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ ሲሆን በጾታ፣ በእድሜ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች እንዲሁ ልዩነት ይኖራል (African Center for Women፣ 1997)"።እያንዳንዱ ባህል ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ ፣ የአመጋገብ ልምዶች አሉት።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ "ሥርዓተጾታ" ብዬ ያቀረብኩት የጾታ ጉዳይ ተፈጥሯዊ የሆነውን ሴትነት/ወንድነት ሳይሆን ባህላዊ ስሪት የሆነውን ሥርዓተጾታ የሚመለከት ነው። በተለይም ማህበረሰቡ ለሴትነት የሚሰጠውን ትርጉም፣ ትርጉሙን ለማጉላት የሚጠቀምበትን ምስል፣ ለሴትነት የሚሰጠውን ማኅበራዊ ሚና እና/ወይም የተግባር ወይም የሥራ ድርሻ (division of labour) እንዲሁም ማኅበራዊ ደረጃ ወዘተ. የሚመለከት ነው።

## 2. ሥርዓተጾታ በጻራ ማኅበረሰብ

በጻራ ሕዝብ ዘንድ፣ በየትኛውም የሀገራችን ክፍል እደሚገኝ ማኅበረሰብ ሁሉ፣ ወንድና ሴት ያላቸው የሥራ ድርሻ፣ ማኅበራዊ ሚናና ቦታ እንዲሁም ማእረግ የተለያየ ነው። ወንድ ሕዝቡን ከፈጣሪ የሚያገናኝናየቅዱስ መንፈስ ማደሪያ እንዲሁም መስዋእት አቅራቢ ነው። ከእናቱ ማህጸን ሲወጣ ጀምሮ የወንድም ይሁን የወንድነት መገለጫ የሆኑ ክዋኔዎች ይደረጉለታል። ክዋኔዎቹ ከጻራ ሕዝብባህልና እምነትየመነጩ የማንነቱ ማሳያዎች ናቸው። ከህጻንነቱ ጀምሮ አመጋገቡ፣ አቀማመጡ፣ጨዋታውና መጫወቻው ውሎው፣ አዳሩ ሁሉ እንደ አባቱ እንዲሆን ይፈለጋል፤አባቱን እንዲመስል፣ አባቱን እንዲያክል፣ አባቱን እንዲተካ፣ በጥቅሉ በአባቱ እግር እንዲቆም በእሱ አምሳል ይሠራል።አባቱንእንዲመስልና እንዲሆን በእሱ ልክና መጠን በባህሉ ይኮተኮታል፤ይታረማል፤ይቀረጻል (ወይም cultivated ይደረጋል)።

ሴት ልጅም እንዲሁ ለሴት ይገባል በሚባል መልኩ በእናቷ ልክና መጠን፣ በእናቷ ማዕረግና ምሥል እንደገና ትቀረጻለች።ይህ የዓይነት ልዩነት ነው ከጾታ ወደ "ሥርዓተ ጾታ" ወይም የኀይል ትስስር የሚያሻግረን።ሽግግሩ ባሕሪን፣ አመለካከትን፣ አስተሳሰብን፣ መብት፣ ግዴታን፣ ሃላፊነትን፣ ወዘተ. የሚያሳይ ነው።ይህ

የባህልኩትኮታና ቀረጻ ከእርግዝና ወቅት ጀምሮ እስከ ሞት ባሉ የሕይወት ዑደቶች ማለትም በእርግዝና፣ በውልደት፣ በማእረግ አሰጣጥ፣ በሞት፣ በመሳሰሉት ልማዶችናሀገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ ሁሉ ይከሰታል፡፡

## 2.1. ጾታና ማኅበራዊ ሚና፤ "ባል ምሰሶ ያቆማል፤ሚስትግርግዳውን ታሳምራለች!"

ቀደም ብለን እንዳነሳነው "ሥርዓተ ጾታ" የሚለው አሰላለፍ ተፈጥሯዊ ሳይሆን ባህላዊና ታሪካዊ የማኅበረሰብ ስሪት ነው፡፡ከርእሱ እንደሚታየው የባል (በጥቅሉ የወንድ) ድርሻ ምሰሶ ማቆም ነው። ሚናው የቤቱንና በቤቱ ወኪልነት ለሚጠሩት የቤተሰብ አባላት ሕልውና መዘርጋት ነው። የኑሯቸው ማእከል ወይም እምብርት መሆን ነው። የሚስት (በጥቅሉ የሴት)ድርሻ ደግሞ የተሠራውን ቤት ማሰማመር፣ ማዘጋጀትና ማድመቅ ነው። ሚናዋ ጉድጉድ ማለትና የጎደለውን መሙላት ነው።

በጻራ ብሄረሰብ ዘንድ ለሴት እና ወንድ የሚሰጠው ማኅበራዊ ሚናእሱን ተከትሎ የሚከሰተው ማኅበራዊ ሃላፊነት የተለያየ ነው፡፡"የተለያየ ነው" የሚለውን በተግባር ለማሳየት ሦስት ምሳሌዎችን ልጥቀስ። ምሳሌዎቹ ከልጆች የዕለት ተዕለት ድርጊት፣ ከባልና ሚስት የቤት ውስጥ ሚና ከመስክ ሥራ እንዲሁም ምግብ እና አመጋገብ አንጻር የቀረቡ ናቸው፡፡ልጆችን ወደሚመለከተው ወደመጀመሪያው የማኅበራዊ ሚና ማሳያ እንለፍ። በየትኛውም ማኅበረሰብ እንደሚታየው ሁሉ የጻራ ልጆች ከልጅነታቸው ጀምሮ በየእለቱ ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሚገባቸው፣ በትይዩ ደግሞ ምን ማድረግ እንደሌለባቸውና እንደማይገባቸው በየጾታቸው አንጻርበተግባር እየተማሩት ያድጋሉ። ሴት ልጅ በቤት ውስጥ እናቷን በማገዝ ታሳልፋለች። ወንድ ልጅ ከአባቱ ጋር በመዋል አባቱ የሚያደርጉትን በማየትና በማድረግ "አደባባያዊ ወግን" ይለማመዳል። ልጁ በአካልና በመንፈስ ጠንከር እያለ ሲሄድ ደግሞ እቤት ውስጥ ከማደር ያልፍና ቆጥ መሳይ በመስራት እደጅ ማደርን ይለማመዳል። ለምን ቢሉ? ድርጊቱ የድፍረትና የጀግንነት መለማመጃ በመሆኑ ነው።

ሴትልጅም እንዲሁ የሴትነቷን ቅርጽ እየመሠረተች ትሄዳለች። የእናቷን ዱካ በመከተል "ማጀታዊውን ዓለም" ትለማመዳለች። በቤተሰብ ውስጥ ከሴቶች ይልቅ የወንዶች ቁጥር ቢበዛ ይመረጣል። "ክብት ሰጥቼው የማይረዳኝ አማች ምን ይሰራል[4]" ይባላል። "ክብት ሰጥቼው" የሚለው ጥሎሽ ማለት ነው፡፡"የማይረዳኝ" ማለት በተለያዩ አጋጣሚዎች ለምሳሌለእርሻ ስራ፣ በሀዘን ወቅት ለማስተዛዘን፣ ሰው የገደለ ለካሳ የሚሆን ክብት ወይም መግዣውን ገንዘብ ቤተሰቡ ወይም አማቾቹ ያዋጣሉ። በእነዚህ የመረዳዳት ሂደት ሴቶች ከጀርባ እንጂ ፊት ለፊት የትብብሩ መሪ አይሆኑም። ይሄውም የመዋጮ እና የስራ ትብብር ውስጥ ሴቶች ለቡድን ስራ አይለመኑም፤ ግን ለስራው መስተንግዶ ምግብ እና መጠጥ ማዘጋጀት ድርሻቸው ነው። ገንዘብ ወይም ክብትበማዋጣት የንብረቱ ባለድርሻ ተደርጋ ስለማትታሰብ ለመስጠትም ለመከልከልም ወሳኙ ወንዱ ብቻ ነው። በዚህና ተያያዥ ምክንያቶች

---

[4] ቃለመጠይቅ፣ አቶ አይከሮ ጊንዳቤ 18/8/2009 ዓ.ም።

በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ የቤተሰብ ቁጥር መብዛቱ ቢወደድም "ሴት ልጅ የሰው ነች፤ ዘሯ ትንሽ ነው፤ የባሏን እንጂ የራሷን ዘር አታበዛም![5]" ስለዚህ አንዲትን ልጃገረድ ሊያጭ የፈለገ ጎረምሳ እንደ መለኪያ ከሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች አንዱ ከቤተሰቧ መካከል ሴት አለመብዛቱ ነው። ከቤተሰቡ አብላጫውን ቁጥር የሚይዙት ወንድሞችና አጎቶቿ እንጂ እህትና አክስቶቿ የሚበዙ ከሆነ አትመረጥም።በተለይ ልጃገረድ ብቻዋን ገበያ ሌላም ቦታ መሄድ የተለመደ አይደለም። ሴት ልጅ የወር አበባ ማየት ከጀመረች አባቷ መኝታ፣ መቀመጫ አጠገብ አትደርስም፤ የምትንቀሳቀስበት ቦታ የተገደበ ይሆናል። ምግብ ታበስላለች እንጂ እናቷ ሳትሰጣት ቢርባትም ወስዳ መብላት አትችልም። ወንድ ልጅ ከራበው ማንም ባይኖር ከተሰራው የቻለውን ያህልበልቶ የበላበትን ሳያነሳ ጥሎ መሄድ የተፈቀደ ነው።

በጻራ ብሄረሰብ ዘንድ ምግብ የራሱ የሆነ ማኅበራዊና ባህላዊ ደረጃ አለው። የሚበላውን መብላት ሲያስመሰግን፣ የማይበላውን መብላት ደግሞ ያስነውራል። ለምሳሌ ያህል አሳ መብላት ለጻራ ብሄረሰብ ቀጻ(ነውር) ነው። ምክንያቱ ደግሞ ባህር ውስጥ የሚኖሩ ነፍሳት አይበሉም የሚል ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ የጻራ ሴቶች የወፍ ዝርያ አይበሉም። ለምሳሌ ዶሮ፣ እንቁላል፣ ቆቅ እና መሰል የአእዋፍ ዝርያን እንስሳትን መመገብ የተለመደ አይደለም። እነዚህን ምግቦች የሚያበስሉት በአብዛኛው ወንዶች ናቸው። ሴቶች ስለማይመገቡ ቅመም መመጠን እሳት ማንደድ ካልሆነ በስተቀር ዶሮ አርዶ ገነጣጥሎ ማጠብ እንቁላል መቀቀል የወንዱ ተግባር ይሆናል። ዶሮ እና እንቁላል በብዛት ወንዶች ልጆች ከቤት ውጭ አብስለው ይበላሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ቦርዴ ተዘጋጅቶ የቤቱ ባለቤት ከመቅመሱ በፊት ማንም አይቀምስም። ሚስቱም ብትሆን ቦርዴውን ታዘጋጃለች እንጂ ከአናቱ መቅመስ አትችልም፤ ነውር ነው። በማንኛውም ቀን የተዘጋጀን ቦርዴ የቤቱ ባለቤት ሳይቀምስ አትቀምስም ለሌላም ሰው አትሰጥም። ቦርዴ ለመሸጥ ያዘጋጀችው ቢሆንም ባል ሳይቀምስ አይሸጥም ምክንያቱም በእሱ ቤት ያዘጋጀችው ቦርዴ የእሱ ነው። ባል ቢሞት እንኳን ወንድ ልጁ ይቀምሳል አለዚያ ወራሽ ዘመዱ ይቀምሳል። መጀመሪያ የተቆረጠም ማር እንዲሁ ባል ሳይቀምስ ሌላ ሰው አይቀምስም። ይህም ልጆች አድገው ባል ወይም ሚስት ሲሆኑ ሚናቸው ምን መሆን እንዳለበት ማስተማሪያ ነው። ሴት ልጅ እናት ሳትፈቅድ፣ ሚስት ባል የሌለበት ወይም ሳይበላ መብላት የተፈቀደ አይደለም። ወንድ ልጅ ያለውን ደፍቶ ቢበላ ግን ነውር የለበትም። ሴት ልጅ ግን አብስላ ለወንድሞቿም ሰጥታ መብላት እንጂ እናት በሌለችበት መብላት አትችልም።

ወንድ ልጅ ለጋብቻ ሲደርስ ሀብት ለማፍራት ተግቶ ይሰራል። የሚሰራው ለጥሎሽ የሚሆን ከብት ለመግዛት፣ በልቡ የፈቀዳትን ልጃገረድ ሌላ እንዳይወስድበት፣ "ቤተሰቧ ሰነፍ ነው" ብሎ እንዳይከለክለው ነው። "ከብት መግዛት ችያለሁ ወይም

5 ቃለመጠይቅ፣ ወ/ሮ ሙላ ሙልጌቲ፣ 6/4/2010ዓ.ም.።

ከብት አርብቻለሁ" ካለ አይኑ የምትገባ፣ ቀልቡ የወደዳትን ልጃገረድ ያማትራል፤ ይመርጣል፣ ያገባል። ሴት ልጅ ለጋብቻ ስትደርስ ቶሎ ለማግባት (ሳታገባ ቀረች ላለመባል) ሊያገቧት በሚፈቅዱ ጎረምሶች አይን ለመግባት ጌጥ ትገዛለች። ጌጡ ለውበት ማድመቂያ፣ ትጉህ ሰራተኛ መሆኗን መጠቆሚያ፣ የሚያጫት ጎረምሳ ማጨት መፈለጉን መግለጫ ከአንገቷ የሚበጥሰው ሀብል መግዣም ነው።

ይህ ለምን ሆነ ስንል ባህሉ የቤቱ የቤተሰቡ ዋና ተጠሪ ወንድ መሆኑን ማሳያ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ማእድ መጀመሪያ የሚቀርበው ወይም የሚበላው ወንድ ነው። እሱ ከባረከው ወይም ከቀመሰ በኋላ ሴቷ ትበላለች መሪው እሱ ሆኖ ተከታይ እሷ ትሆናለች። ይህን ማለማመድ የሚጀመረው ደግሞ በልጅነት ነው። የሥርዓተ ጾታው መሠረት የሚጣልበት ህጻንነት ነው። ይህ አልፎ ሀላፊነት መውሰድ፣ ወንድ ባል ሴት ሚስት ስትሆን ይህንኑ ልማድ እያሳደገች ሄዳ የባህሉ ጠበቃ ትሆናለች፤ ትኖረዋለች፤ ታስተምረዋለች።

ሁለተኛው ከባልና ሚስት የቤት ውስጥ ሚናአንጻር የሚታይ ነው።ምሰሶ (ቤት) የወንድ ነው። ምሰሶ የሚቆመው ባል እስካለ ብቻ ነው፤ ከሞተ ቤቱም አብሮ ይሞታል። ሴትና ወንድ ባል እና ሚስት ሆነው በአንድ ጎጆ ሲኖሩ ጎጆው ዋናው መዋቅሩ በባል ይሰራል። ሚስት የኋላ በር መግጠም፣ መሬቱን ጣራ ግርግዳውን ማሳመር የቤት ውስጥ ቁሶችን ማሟላት ድርሻዋ ይሆናል። የኋላ በር ሌላው የቤተሰቡ አባልም ለመውጫ ለመግቢያ ቢገለገልበትም ዋና አላማው ባል ሲደበድባት ማምለጫ ነው፤ ተብሎ ስለሚታመን በሩን አበጅታ የምትገጥመው ሚስት ነች። Fiorenza የተባሉ የሥርዓተ ጾታ ተመራማሪ ባንድ ወቅት"...maleness is the norm, while femaleness constitutes a deviation from this norm. He is the subject, the absolute. But she is the other" (1986:42) በማለት የገለፁት ይህ ዓይነቱን ሁኔታ ነው። ወንዱ የባህሉ ባለቤት በመሆኑ ለባህሉ ቀዋሚ ወግ ነው፡፡ ሴቷ ደግሞ ለዚያ ቋሚ ባህል ባዕድ በመሆኗ ከዚያ ቀዋሚ ወግ በትይዩ ናት፡፡ ምክንያቱም ሴቷ ከወንዱ አንጻር እንጂ በራሷ ማንነትና መንገድ (in her own right) የምትገለጽበት ሁኔታ የለም።

ሌላኛው ከዚሁ ከምሰሶ ጋር የተያያዘው በጻራ ማኅበረሰብ ዘንድ የወንድና የሴት ወይም የባልና ሚስት የቡና ሾርቃ (ስኒ)የተለያየ መሆን እና የአጠጣጥ ልማዱ ነው። ባል ቡና ሲጠጣ ከአናቱ ለውቃቢው ደፍቶ ነው። ምክንያቱም እሱ ባለምሰሶ ነው። ሚስት ግን አትደፋም፤ የራሷ ምሰሶ ወይም ውቃቢ የላትምና። ስለዚህ ለማን ትደፋለች? ጉዳዩ ወንድ የመሆን ብቻ አይደለም። ባለቤት የመሆን ጭምር እንጂ። ለምሳሌ ሌላ ወንድ በእንግድነት ወደተጠቀሰው አባወራ ቢመጣና ቢሰነብት ስኒ ሊደፋ አይችልም። ምክንያቱም እንግዳው ወንድ ቢሆንም የቤቱ ባለቤትና ባለምሰሶ አይደለም።

በባልና ሚስት መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ሴቷችላ እንድትኖር ይበረታታል። ሴት ልጅ ባልዋን ተቀይማ ከቤቷ ወጥታ ማደር አትችልም።ባል ሚስቱን መደብደብ

እንደ መብቱ የሚቆጠር ልማድ ሲሆን ተደበደብኩ ብላ ወደ ቤተሰቧ መሄድ ተጨማሪ ዋጋ ያስከፍላታል። የባል ድብደባ በደል የሚሆነው ከደማች ወይም አካሏ ከጎደለ ብቻ ነው።የሴቷ ቤተሰብ አንዲት ሴት ልጃቸው ተድራ ከሄደች በኂላ ከባሏ ተጣልታ ተበድላም ቢሆን ተመልሳ ወደ እነሱ እንድትመጣ አያበረታቱም። ከሄደችባቸውም አባቷ ቶሎ ወደ ቤቷ እንድትመለስ ማግባባት ካልሆነም አስገድዶም ቢሆን ጎረቤቶቿ ዘንድ እንድትሄድ ያደርጋል።ምክንያቱም አንዲት ሴት ልጅ ካገባች በኂላ ጥሎሽ የከፈለባት ባሏ እና የእሱቤተሰብ እንጂ የወላጆቿ አይደለችም። ስለዚህ ወደ ቤተሰቧ ተመልሳ የምትሄደው ሲታመሙ ለመጠየቅ ሀዘን ሲኖር ለማስተዛዘን ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ አባት እናቷ ጣልቃ ገብተው ችግሯን መስማት፣መፍትሄ መስጠት የተለመደ አይደለም።ምክንያቱም “ባል” ወይም በጠቅላላው “ወንድ” ማዕከል በሆነበት በዚህ የባህል ዓለም ውስጥ ሴት ልክ ብትሆንም ተቀባይነት ሊኖራት አይችልም። ባሏን ወይም ወንድን እንድታስተምርና ከስህተቱ ልትመልሰው አትችልም። ምክንያቱም ሴት በወንድ ላይ ትሰለጥን ዘንድ አይቻላትም። ይህን ማድረግ “ነውር” ወይም “ፀያፍ” ድርጊት ነው።

ከዚህ አልፎ ፍቺ ላይ ከደረሱ ጉዳቱ የሴቷ ያመዝናል። ምክንያቱም ሚስት ወደ ቤተሰቧ ስትመለስ ያፈራችው ንብረት ቢኖርም ምንምይዛመሄድ አይፈቀድላትም። እንዲያውም አባቷ የወሰደውን ጥሎሽ ለባሏ የመመለስ ግዴታ አለባት። በተጨማሪም አንድ ሴት አግብታ ከተፋታች በኂላ ሌላ እንዳታገባ የሚከለክል ባህላዊ ደንብ ባይኖርም ሊያገባት የሚፈልግ ወንድ የቀድሞ ባሏን ፍራቻ ለማግባት አይደፍርም።ደፍሮ የሚያገባ ካለ የሚፈጠረውን አንባ ጓሮ ለመቻል እና የቀድሞ ባሏ ለአባቷ ሰጥቶ የነበረውን ጥሎሽ ለመመለስ ወስኖ መሆን አለበት።

የማህበረሰብን ተሳትፎና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ሲገጥሙ በዋነኝነት ሀላፊነት የሚወስዱት፣ የሚወስኑት መፍትሄ የሚሰጡት ወንዶች ናቸው። ለምሳሌ በሁለት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል ግጭት ቢፈጠር አሸማጋዮቹ ወንዶች ናቸው። ሴቶችበዕርቅስርዐትላይየማሸማገልሚናየላቸውም።
ተሸምጋይዋሴትከሆነችበደሏንመናገርካለባትበሽምግልናውዕለትተቀርባታስረዳለች። ሆኖም ሰው የገደለ ከገዳይ ጋር ለመታረቅ ይቅር ለመባባል እና ቂም እንዲሽር ለማድረግ የግድ ልጃገረድ በስጦታ ለሚች ወገን ትሰጣለች።የምትሰጠው ልጃገረድ “ቆጸኒያ” ትባላለች።

የሟች ወገኖች የእርቁ ሂደት መቋጫ በሆነው ክዋኔ ፍጻሜ “ቆጸኒያ”ን ይዘው ይሄዳሉ። ለጋብቻ ስትደርስ ሟቹ ትልቅ ሰው ከሆነና ወንድ ልጅ ካለው እሱ ያገባታል፤ አግብቶም ከሆነ ሁለተኛ ሚስት ትሆናለች።ሟቹ ያልወለደ ከሆነ ወንድሙ፣ ወንድም ከሌለው ዘመዱ ያገባታል። የገዳይና ሟች ወገን መጋባት የማይችሉ ዘመዳሞች ከሆኑ ስታገባ ጥሎሽ ይወስዳሉ።ወንድ ልጅ ለሟች ካሳ የማይሰጠው ወላጆቹን እንጂ የሟችን ቤተሰብ ስም አይጠራም፤ ሴት ግን በምትወልደው ልጅ አማካይነት ያገባችውን ቤተሰብ ስም ታስጠራለች፤ የሟቹን ምትክ ወልዳ የጎደለውን ታሟላለች ተብሎ ነው።

ሦስተኛው ማኅበራዊ ሚናከመስክ ሥራ አንጻር የሚቀርብ ነው።በመስክ ሥራ፣ ሥር ከምናያቸው ጉዳዮች አንዱ የእርሻ ስራ ነው።በእርሻ ሥራ ወቅት ከምንጣሮ ጀምሮ በአብዛኛው በወንዶች ቢሰራም በከፊል ሴቶች ይሳተፋሉ። እነዚህ ሴቶች ባል የሌላቸው፣ ቤተሰባቸውን የሚያግዙ ልጃገረዶች ከምንጣሮ ውጭ በሆኑ በጉልጓሎ፣ ቁፋሮ፣ ዘር መዝራት በማንኛውም የእርሻ ስራ ላይ ይሳተፋሉ። ጎተራ የወንድ፤ ምድጃ የሴት ነው። ሴት ጎተራ መንካት አትችልም። ወንዱ ምርቱ እንደደረሰ ጎተራ ሳይገባ ለቤተሰቡ ያስፈልጋል ያለውን ይሰጣታል። ሚስት የሰጣት ሲያልቅ ማለቁን ትናገራለች እንጂ ጎተራ ከፍታ እህል አትነካም። በየእለቱ ምግብ ማብሰል ማቅረብ የሴቷ ድርሻ ነው። ወንድ ምድጃ አጠገብ አይደርስም፣ መኝታው መመገቢያው ማረፊያው ከምሰሶ በላይ ሲሆን ምድጃው ደግሞ በሴቷ መኝታ አጠገብ ከምሰሶ በታች ነው። ንብ ማነብ ወንዶች ከቀፎ ሰቀላው እስከማር ቆረጣው ከዚያም ለገበያ ማቅረብ ስራቸው ነው።

የጓሮ አትክልት፣ ቅቤ፣ አይብ፣ በጥቅሉ የእንሰሳት ተዋጽዎን ሴቶች ይሸጣሉ። እህል በተለይ ጤፍ ከብት፣ ማር ለገበያ የሚያቀርቡት ወንዶች ናቸው። ማር ወይም እህል አንድ ወንድ ለሚስቱ እንድትሸጥ ከሰጣት ግን ልትሸጥ ትችላለች።

## 2.2. ሥርዓተጾታና ሀገረሰባዊ እምነት

ከተፈጥሮ ጋር ከተያያዙ ሀገረሰባዊ እምነት (ለምሳሌ ከመሀንነት፣ ከወር አበባ መፍሰስ)፣ ከአኗኗር ልማዶች ጋር ከተሳሰሩ ለምሳሌ ከዝሙት ከእርኩስ መንፈስ ጋር ተያይዘው ከሚቀርቡ ጉዳዮችና እነሱን ተከትለው ከሚመጡ እንደ እርግማን፣ ከበደል መንጻት ከመሳሰሉ ተግባሮች አንጻር ሊቀርብ ይችላል።

### 2.2.1. ኪቻ (የወር አበባ) "እስከምትነጻ ጓሮ ውላ ትደር!"

በማኅበረሰቡ ዘንድ "ኪቻ"(የወር አበባ) ላይ ያለች ሴት ከተፈቀደላት ቦታ ውጭ መገኘት የተከለከለነው።በጻራ ብሄረሰብባህል መሠረት ኪቻ ላይ ያለች ሴት እስክትነጻ ድረስ እንድትቆይ፣ ከተፈቀደላት ቦታ ውጭ መገኘት፤ እንዳትነካ የተከለከለችውን ቁስ መንካት ክልክል ነው። አንዲት ሴት ኪቻ ላይ በምትሆንበት ጊዜ እስከምትነጻ (ቢያንስ አምስት ቀን) ድረስ ከተለያዩ የየእለት ተግባራት እና የመንቀሳቀሻ ቦታዎች ትወሰናለች፣ ትከለከላለች። ይህ ልማድ ለማንኛዋም ሴት ተመሳሳይ ደንብ ነው። ለምሳሌ አንድ ሙሽራ ባሏ ቤት በገባችበትእለት ኪቻ ቢመጣ ከቤት ትወጣለች ፤ አንዲት ልጃገረድከቤቷ ወጥታ የማታውቅ የመጀመሪያውን ኪቻ ብታይ ቤት አታድርም። የቤቱ እማ ወራ በቤት ውስጥ ወሳኝ የሚባል ስራ ላይ እያለች ኪቻ ከመጣትታው ትወጣለች። ከኪቻ እስከምትነጻ ባሉ ቀናት ከመኖሪያ ቤት ውጭ ጓሮ ውላ ታድራለች። ቤቷ መግባት፣ በተለይ በባሏ መኝታ አጠገብ ማለፍ፣የሚበላበትን ምግብ የሚበስልበትን በጥቅሉ ምሰሶ ያቆመበትን ቤት መርገጥ፤ ኤቀትሳ(የትውፊታዊ እምነት መሪ) ባለበት መሄድ ክልክል ነው። በወር አበባ ወቅት ሴት የምታርፍበትን ጎጆ ባል አይሰራም።

ባል ለሚስቱ ማረፊያ ጎጆ ቢሰራ ቆሌው(መንፈሱ) ይቆጣል። ምክንያቱም ባል ቤት ሲሰራ በቤት ውስጥ የእሱ ቆሌይኖራል። የእሱ ቆሌ ደግሞ የወር አበባ ደም ይጠላል፤ ስለዚህይቆጣል፤ ይቀጣል። ወንድ ልጅ ያላት እናት ልጇ ማረፊያ ጎጆ ይሰራላታል። አለዚያ ለራሷ የሚሆን ከለላ ሰርታ በዚያ ታድራለች። በቃለመጠይቅ ‘ልጅ ካላት ወይም ካለኝ ይሰራል’ ይበሉ እንጂ በምልከታ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት ከአምስት እናቶች አንደኛቸውም ጎጆ የላቸውም። ጥላ ባለውና የተደላደለ መሬት ፈልገው በዚያው ውለው ያድራሉ። በበጋ ወራት እንደ ቤት ባይሆንም ችግሩ የጎላ አይሆንም፤ በክረምት ወራት ግን ይቸገራሉ። በኪቻ ላይ ላለች ሴት ለባሏ እና ለልጆቿ በጎረቤት የሚገኙ ሴቶች ምግብ ያበስላሉ። ይህችም ሴት በሌላ ጊዜ ብድሯን ትመልሳለች። ሴቶች በወር አበባ ላይ ሲሆኑ ቤታቸው መቆየት እንደሌለባቸው ያምናሉ፤ ይህን በተመለከተ በቡድን ውይይት ላይ የተነሳው የሴቶቹን እምነት የሚያሳየው ሀሳብ ተከታዩ ነው።

> ኪቻ ሲመጣ ኤቀቀረንቤ (የወር አበባ መጥቶ ከቤት ወጣሁ) ወይም “አንዲረትሳ” ብለን ከቤት እንወጣለን።ሴት ልጅ ያለቻት ልጇ፣ አለዚያ ጎረቤት ሴት ምግብ ትሰጣታለች። ቀን ቀን ጓሮ ያለ አትክልት ስናርም፣ ስንኮተኩት እንውላለን። ማታ ቤት መሳይ ጓሮ ውስጥ እናድራለን። በኪቻ ላይ እያለን ከመኖሪያ ቤታችን ባንወጣ ባላችን ሊታመም አይኑ ሊጠፋ ሲከፋም ሊሞት ይችላል። ወይም መብረቅ ቤታችንን ሊመታው እና ሳትወጣ የቀረችው ሴት ልትሞት ትችላለች ተብሎ ይታመናል። ሳይወጡ ቀርተው ሞተዋል የሚባሉ ሴቶችን ታሪክ ሰምተናል። ስለዚህ በዚህ ምክንያት ዘራችን እንዳያጥር፤ ልጆቻችን ያለ እድሜያቸው እንዳይቀጩ፤ ለቤተሰቡ ስንል ባይመቸንም ቢበርድም ደጅ ማደር ቢያስፈራም አምስት ስድስት ቀን እንቆያለን። ኪቻ መምጣቱን ደብቀን ማንም አያውቅም ብለን በቤታችን ብንቆይ ወይም ኤቀትሳ ባለበት ብንሄድ ቆሌው ያውቃል። የሚያውቀውም ባል ሲበላም ሆነ ሲጠጣ ከአናቱ ጥሎ ወይም ረጭቶ ‘የአባቴ አምላክ እኔ ክፉ የሚያደርግብኝን አላውቅምና አንተ የሚያደርጉትን፣ የሚያስቡትን ታውቃለህና ለእኔ ያሉትን ክፉ ለራሳቸው አድርግ’ ብሎ ነው፤ ያለው ደግሞ ይደርሳል።[6]

አንዲት የወር አበባ ላይ ያለች ሴት ከማይፈቀድላት ቦታ ውጭ መገኘት አይቻልም ብላ አጥብቃ ታምናለች። ይህን ልማድየተከለው ደግሞ ሀገረሰባዊ እምነቱ ስለመሆኑ ማሳያውልማዱን ብተላለፍ ከላይ የተጠቀሱት እና ሌላም የከፋ ችግር ሊደርስብኝ ይችላል ብላ ማመኗ ነው። ቅጣቱ በወር አምስት እና ስድስት ቀን እደጅ ከማደር የከፋ ስለሆነ በወር አበባ ላይ እያለች እንዳትነካ እንዳትረግጥ ከተከለከለችበት ሁሉ ትታቀባለች። አልፋ ተርፋምልጆቿም ይህን እንዲያውቁ ምንም ከለላ በሌለበት እያደረች፣ ‘የት ታድሪያለሽ’ ስትባል ‘ጓሮ ጎጆ አለ’እያለች በወጉ ከለላ እንኳ በሌለው ሜዳና ጫካ ታድራለች። ስለዚህ የባህሉ አስቀጣይ ሴቷ ራሷ ነች።

---

[6]የቡድን ውይይት፣ አንገላ ቀበሌ 29/3/2010 ዓ.ም።

አንዲት ሴት ኪቻ ላይ መሆኗን ደብቃ ቤቷ ብትቆይ ልምድን ከማፍረስ ባለፈ እንደ ጥፋት ተቆጥሮ በተለይ ከባለቤቷ ጋር ያለሶስተኛ ወገን የማይፈታ ግጭት ውስጥ ትገባለች። ወዲያው ባይታወቅም ቆይቶ መታወቁ አይቀርም ተብሎ ይታመናል። ባሏ ይህንን ካወቀ ለሽማግሌ እና ለኤቀትሳ[7] ይከሳታል። ሽማግሌ ተቀምጦ በዳይ የተባለችው ሴት እያወቀች ቀጻ ስለሰራች ቤቷንና ባሏን፣ ኤቀትሳን፣ የሞቱትን የባሏን ዘመዶች መንፈስ አስነውራለችና "መሳ"(ታንጻ)የሚል ውሳኔ ይወሰንባታል። የመሳ ስርዓት፤ የሚወስኑት ሽማግሌዎች ሲሆኑ ሰአቱ እና ሂደቱ የሚታወቅ ደንብ አለው።መሳ ንስሀ እንደመግባት ይቆጠራል። በእሷ ምክንያት የረከሰውን ለማንጻት ሶስት የንብ ቀፎ ከነንቡ ማቅረብ አለባት።

የንብ ቀፎ የሚሰቅሉ ወንዶች በመሆናቸው ወላጆቿ ወይም ቀፎ የሰቀለ ልጅ ካላት ይሰጧታል። ባሏ ግን ቢኖረውም አይሰጣትም። ስለዚህ የንብ ቀፎ በስጦታ የሚሰጣት ካጣች ትገዛለች። በቀጠሮ እለት ዋዜማ ሶስት የንብ ቀፎ ከነንቡ የሰጧት ወይም የሸጡላት አምጥተው በቤቷ ደጃፍ ያሳድራሉ። በማግስቱ በማለዳ ውሳኔውን የወሰኑ ሽማግሌዎች ባሏ እንዲሁም የመሳ ክዋኔ መሪ፣ በተገኙበት ይፈጸማል። ክዋኔውም፤ አንድ የንብ ቀፎ ከፋች የስጋ ዘመዷ እንዲሁም ባለቤቷ በማለዳ በቤቷ ደጃፍ ይገኛሉ። ከተዘጋጀው ሶስት ቀፎ ንብ አንዱ በዚሁ በቤቷ ደጃፍ የሚከፈት ይሆናል። የመጀመሪያው ቀፎ ሲከፈት፣ ሴትየዋ ቤቷ ደጃፍ፣ ንቦቹ ከቀፎ ሲለቀቁ ያርፉብታል ተብሎ በሚገመትበት አቅጣጫ ትቆማለች። ቀፎውን ለመክፈት የተዘጋጀው ዘመዷ ፊት ለፊቷ ይቆማል። በቅድሚያ የሚከፈተውን ቀፎ ለመክፈት ዝግጁ አድርጎ በመካከላቸው ዘመዷ የሆነው ግለሰብ አስተካክሎ ያስቀምጣል። ሽማግሌዎች ሲያዙት ቀፎውን ይከፍተዋል። ከቀፎው የወጡ ንቦች ሴትየዋ ላይ ያርፋሉ። ሴትየዋ ባለችበት ሆና ንቦቹ ነድፈው እንዳይጎዷት መከላከል ትችላለች። ሆኖም መሸሽም ሆነ ሌላ ሰው ንቦቹ እንዳይጎዷት መከላከል አይፈቀድም። በዚህ መልኩ ባሏን አነጻች ማለት ነው። ሁለተኛው ቀፎ ዘመዷ ይዞ ባልየውና ሽማግሌዎችም አብረዋት ኤቀትሳ ቤት ይሄዳሉ። በቤቱ ደጃፍ ላይ በተመሳሳይ መልኩ የንብ ቀፎው በእሷው ዘመድ ተከፍቶ ታነጻለች። የመጨረሻው ለሙት መንፈስ መስዋእት ለማቅረብ ስልጣን ወደ ተሰጠው "ኳሽትሳ" ዘንድ በመሄድ የሞቱትን የባሏን ዘመዶች መንፈስ በቀረው አንድ ቀፎ ንብ ታነጻለች። ይህ ስፍራ ለሞቱ የባሏ ዘመድ የሆኑ ወንዶች መንፈስ መስዋእት የሚቀርብበት ነው። በዚህ ስፍራ በቤቷ እና በኤቀትሳው ደጅ እንደተደረገው የቀረውን አንድ ቀፎ ንቦች በቆመችበት ወይም በተቀመጠችበት በመልቀቅ ማንጻቱ ተፈጽሞ ባዶው ቀፎ ለባለቤቱ ይመለሳል። ሴትየዋም በሽማግሌዎቹ እና በኤቀትሳው ተመርቃ ወደቤቷ ትመለሳለች።[8]

ከማንጻቷ በፊት ህመም ከነበረባት ትፈወሳለች እንዲሁም ከደረሰባት ማንኛውም እክል ትወጣለች ተብሎ ይታመናል።በአጠቃላይ ኪቻ ላይ ያለች ሴት ከምትነካው

[7]የትውፊታዊ እምነት መሪ(ፍሬህይወት 2019)።
[8]ምልከታ፤ ወ/ሮ ሪዎቶ ታጁቴ ቤት 23/3/210ዓ.ም. በተፈጸመ የማንጻት ሥርኣት ላይ አጥኚዋ የተሳተፈችበት።

ይልቅ የማትነካው ይበልጣል። ለምሳሌ እንደ ምሰሶ አይነት ድንገት ብትነካው ተመልሶ ምሰሶ የሚለውን እሳቤ ለማግኘት ማንጻት ያስፈልጋል። አለዚያ ቤቱ እንደረከሰ ይቆጠራል። በእርግጥ ሴት የሚፈሳት ደም ሁሉ እንደ ኪቻ አይታይም። ለምሳሌ አንዲት ሴት ስትወልድ በቤቷ ውስጥ ነው። ስለዚህ ደም እየፈሰሳት በቤት ውስጥ ትቆያለች ማለት ነው። የእንግዴ ልጁ በዚያው ቤት ውስጥ የሚቆይ ሲሆን እንዲያውም ባል መቅበሪያውን ጉርጓድ ቆፍሮ እሷ ትከታለች እሱ አፈር መልሶ እንግዴ ልጁን ይቀብራል። ምክንያቱ ደግሞ "ልጅ ወልዳ የሚፈሳት 'ናኤሱታ' (የአራስ ደም)" ተብሎ ከኪቻ ተለይቶ ርኩሰት እንደሌለበት ይታመናል።

ልክ እንደ ኪቻ ሁሉ ሴት ልጅ "ዶላ"(እባጭ) ብልቷ አካባቢ ከወጣባት ከቤት መውጣቷ ግዴታ ነው። ይህ ህመም ያለባት ሴት ከቤት አለመውጣት አትችልም፤ ምክንያቱም ሁኔታው በማኅበረሰቡ ዘንድ እንደ እርኩሰት የሚታሰብ የበሽታ አይነት ነው። አንዲት ሴት ልክ ለኪቻ ከቤት እንድምትወጣው ለዶላም ከቤት ወጥታ እደጅ (ጓሮ) ትኖራለች። ምክንያቱም እሷ ከቤት ካልወጣች ቤቱ ይረክሳል፣ባሏም ሊሞት ይችላል። ህመሙ ጸንቶ በዚሁ ሳቢያ ከሞተችም በዚያው ወደ ቀብር ትወሰዳለች። ልጆች ካሉ ከለላ ይሰሩላታል። ባል እንደኪቻው ሁሉ በዚህ ህመም ለተያዘች ሚስቱ የምታርፍበት ቤት መስራት አይችልም። ምክንያቱም ባሏ ምሰሶ አቁሞ ከሰራ በዚያስፍራ ላይ የእሱ ቆሌ(መንፈስ) ይኖራል። የባል ቆሌ[9] ደግሞ እንደ ዶላ እና ኪቻ ያሉትን ይጠላል። ስለዚህ ባል ሚስቱ የምታርፍበትን ቤት መስራት እምነቱ ያግደዋል።

### 2.2.2."እንደ ማሪያም[10]"

በጻራ ብሄረሰብ ትውፊታዊ እምነት የለያዩ የሚከበሩ መንፈሶችበስም ተለይተው ይታወቃሉ። ለእነዚህ እንደየደንባቸው መስዋእት የሚያቀርቡ ከጻራ የተመረጡ ጎሳዎች ተወካይ ወንዶች አሉ። "በሴት ጾታ የሚጠራ መንፈስ የለም" ይበሉ እንጂ ገራትሳ የሚባሉ በትውፊታዊ እምነት ውስጥ የሰዎችን ችግር መንስኤውን እና መፍትሄውን ያውቃሉ ተብለው የሚታመንባቸው ሴቶች እንደ ማሪያም የሚል መንፈስ እንዳላቸው በተለያዩ መረጃዎች ውስጥ ለማረጋገጥ ችያለሁ።

"ማሪያም" የሚሉት በሴት ጾታ የምትታወቀው መንፈስ በብዛት የሚጠሩት በወሊድ ወቅት፣ ምጥ የጸናባትን ሴት እንድትረዳትመለማመኛ ነው። እንዲሁም ልጅ የሌላቸው እንዲያገኙ ስእለት የሚሳሉት ለማሪያም ሲሆን ከደረሰላቸው

[9]ቆሌ ማለት በአባወራ ላይ የሚያድር ቅዱስ መንፈስ በቀዬው በሰፈሩ አብሮት የሚኖር የሚጠብቀው በአይን የማይታይ እንደሆነ ይታመናል። አንድ አባ ወራም በቤቱ በሰፈሩ ምግብ ሲበላ ከእናቱ ለቆሌ ብሎ ይጥላል። መጠጥም ሲጠጣ እንዲሁ። ይህ መንፈስም የሚጠላቸው እና የሚያስቆጡት ከተደረገ ለምሳሌ የወር አበባ ላይ ያለች ሴት ቆሌው በማይፈቅደው ቦታ መገኘት ያስቆጣዋል፤ ሲከፋም ይቀጣል ስለዚህ ጥንቃቄ ይደረግለታል። ጥፋትንም አውቆ ይቅርታ መጠየቅን የሚያስገድድ መንፈስ ነው።

[10]የመግባቢያ 'ኮድ' ነው። ቅሬታን፣ እርግማንን፣ ቁጣን መለማመኛን የሚጠቀም ሀረግ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከምትታወቀው የእየሱስ እናት ማሪያም ጋር ግንኙነት ያለው በሩቁ ነው። በሩቅ ማለቴ ሀሳቡ የተያያዘና የተገናኘ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ሆኖም ይህ ሌላ ጥናት ይፈልጋል።

የሚከፍሉትግ ገራትሳ ተብለው ለሚታወቁት ሴቶች ነው። የዚህ እሳቤ ግለሰቧን ሳይሆን እሷ የሰዎችን ችግር እንድታውቅና መፍትሄ እንድትሰጥ የሚያደርጋትን መንፈስ መኖሩን ጠቋሚ ነው። ለዚህ ማሳያው በኤቃ እምነት፤ ሴት "ነይ ማርያም" ካለች ቁጣን፣ መቁረጥን፣ ማምረርን ጠቋሚ ነው። ትርጉሙ አንተን የፈጠረችህ ማሪያም እንደማለት ነው። "እንደ ማሪያም" የሚለው መንፈስ ስለመሆኗ ሌላው መሳያ ባልና ሚስት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር የሚመላለሷቸው ዘለፋ፣ ስድብ ወይም እርግማን መካከል "የአንተ ወይም የአንቺ ማሪያም" እንዲህ ወይም እንዲያ ታድርግህ ወይም ታድርግሽ የሚለው ተራ ስድብና ዘለፋ ሳይሆን እርግማን ነው። ለምሳሌባል ሚስቱን እህል እየፈጨች ሳለ "የኔ ማሪያም የምትፈጪውን አታስበላሽ" ቢላት በማሪያም ስም  እረግሞኛልና ከዚህ እህል አልቀምስም ትላለች። ሚስቱ ለሀገር ሽማግሌ እንዲሁም ለኤቀትሳ ትከሰዋለች። ካሳው እና ይቅርታው ሚስቱን ብቻ ሳይሆን የተሰደበችውን ማሪያም ይቅርታ መጠየቅ የግድ ነው። ለዚህ አይነቱ ክስ እርቅ ለማውረድ የተለየ ክዋኔ አለው። ስለዚህ ለሴትም ሆነ ለወንድ ማሪያም የሚለው በሴት ጾታ የምትታወቅ የምትከበር የምትፈራ መንፈስ እንደሆነች ማሳያ ነው።

ሌላው ገራትሳ በመባል የሚታወቁ ሴቶች ያሉ ሲሆን በተሰጣቸው ልዩ ችሎታ ለተጠየቁት ጥያቄ በላያቸው ያደረች መንፈስ በሚያፈሱት ውሃ አማካይነት ምላሽና መፍትሄውን ትገልጽላቸዋል።ገራትሳ የሆኑ ሴቶች እንደ ኤቀትሳ ኤቀኬታ ወይም የተለየ ቤት የላቸውም። እንደ ሌሎቹ ሴቶች የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች ጠብቀው በቤታቸው ይኖራሉ። ባለጉዳይ የሆኑ ሴቶችም ወንዶችም ለራሳቸው ወይም ለቤተሰባቸው ችግር መፍትሄ ፍለጋ ገራትሳዋ ቤት በመሄድ መፍትሄ ይጠይቃሉ። ገራትሳም ለጥያቄያቸው ምላሽ ትሰጣለች፤ ለዚህ ተግባሯም ከአስር ብር ያልበለጠ ገንዘብ ትቀበላለች። ከእያንዳንዱ ባለጉዳይ ከተቀበለችው ገንዘብ ላይ እየቀነሰች በማጠራቀም ፈቃድ ለሰጣት ኤቀትሳት ከሰጠች በኋላቀሪውንየፈለገችውን ልታደርግ ትችላለች። ገንዘብ የማትቀበልበት ጊዜም ይኖራል፣ ይሄውም ስለታመመ ሰው መፍትሄ ተጠይቃ የታያት ታማሚው እንደሚሞት ከሆነ የታያትንም አትነግርም ገንዘብም አትቀበልም።

### 2.2.3. "መካን ሴት በመካን ማሰሮ"

መካንነት እና/ወይም የወር አበባ መፍሰስ ተፈጥሯዊ እውነታ ነው። ነገር ግን "መካን ሴትን በመካን ማሰሮ" በሚል የሚደረገው እንደ እርግማን ያሉ ድርጊቶችና እርግማኑን ለማንጻት የሚፈጸሙ እንደ ማንጻት ያሉ ክዋኔዎች የማኅበራዊና ባህላዊ ልማድ ውጤቶች ብቻ ሳይሆኑ የሀገረሰባዊ እምነት መሰረትም አላቸው።

ባልና ሚስት መውለድ ካልቻሉ ምክንያቱ "ሴቷ ላይ የሚያድር መጥፎ መንፈስ ፍሬ እንዳታፈራ አድርጓት ነው" በሚልየእምነት ጣጣ ተደርጎ ይቆጠራል። ምክንያቱም "መካንነት የሴቶች ፍሬ ያለማፍራት ነው" እንጂ የወንዱ እንዳልሆነ ይታመናል። ለምን ቢባል ፍሬ የሚያፈሩ (የወር አበባ የሚያዩ) ሴቶች ስለሆኑ ነው። ስለዚህ አንድ ሴትና ወንድ ተጋብተው ልጅ ባይወልዱ ወንዱ ሌላ ሴት ያገባል። የማግባቱ

ምክንያት ሚስቱ ፍሬ ማፍራት ባለመቻሏ ሲሆን ሁለተኛ ያገባት ሚስቱም ፍሬ ካላፈራች ሌላ ያገባል እንጂ እሱም ሆነማህበረሰቡ ላለመውለዱ መካንነት የወንዱ ተፈጥሮ ሊሆን ይችላል ተብሎ አይገመትም።

ሴትን መካን የሚያደርግ መጥፎ መንፈስ በህይወት እስካለች አብሯት ይኖራል። ስትሞት ወደ ሌላዋ ሴት እንዳይሄድ ከእሷ ጋር እንዲጠፋ በሸክላ ተመስሎ ይሰበራል። የሚሰበረው ሸክላ ማሰሮ ሲሆን ከተሰራ ጀምሮ ምንም አገልግሎት ያልሰጠ መሆን አለበት። ይህንን ሁለት ማሰሮ መካን መሆኗን አምና ተቀብላ የምትኖረው ሴት ወይም ቤተሰቧ ይገዛሉ። በምትኖርበት ቤት ከሌላው ተለይቶ "የመካን ማሰሮ" ተብሎ ሰው በማይነካበት ቦታ በቤት የውስጥ ጣራ ላይ ተሰቅሎ ይቀመጣል። ይሄ ማሰሮ መካን ሴት ሞታ አስከሬኗ ከመኖሪያ ቤቷ ወደ ቀብር ቦታ ሲሄድ እሷን መካን ያደረገን መንፈስ ለማባረር ሁለቱ ማሰሮ አብሮ ከቤት ይወጣል። ይሄም መንፈሱ በአዲስ ሸክላ ተመስሎ እንዲሞት እንዲጠፋ ሸክላው ከአስከሬን ጋር ቤተሰቧ በቤቷ በር ላይ አንዱ ይሰበራል። ሁለተኛው ከተቀበረች በኋላ ዳገታማ ስፍራ ፈልገው ከዳገት ወደ ቁልቁለት ያንከባልሉታል። የሸክላው ስብራት መጥፎው መንፈስ በአካባቢው በሌሎች ሴቶች ላይ እንዳያድር መስበር ማለት ነው። ተምሳሌትነቱ እሷም ፍሬ ሳታፈራ እራሷን ሳትተካ እንደሄደችው ሁሉ ማሰሮውም ተሰርቶ አገልግሎት ሳይሰጥ ኖሮ ተሰበረ ለማለት ነው። የዚህ አንድምታ መካን የሆነችው ሴት ብትሞትም መካን እንድትሆን የተጸናወታት መንፈስ አይሞትም፤ ስለዚህ ወደ ሌሎች ሴቶች ሊሸጋገር ይችላል ማለት ነው።

## 2.3. ሥርዓተጾታ እና ነውር(ቀጻ)

ነውርበጻረሳ "ቀጻ"ተብሎ ይታወቃል። ነውር የሚባለው በአንድ ማህበረሰብ ባህልና እምነት መሠረት እንደ መጥፎ ነገር የሚታይና የሚቆጠር ልማድ፣ ድርጊት ወይም ተግባር ነው (አማርኛ መዝገበቃል፣ 2006፣ 282)። የጻራ ብሄረሰብ አንድ ግለሰብ አውቆም ይሁን በስህተት ማህበረሰቡ ቀጻ ያለውን ፈጽሞ የተገኘ እንደሆን ከዚያ ቀጻ የሚነጻበት ሥርዓት አለው። ይህም ማለት አንድ ሰው ቀጻ ሰርቶእንዳልሰራ ዝምአይልም። ምክንያቱም "ቀጻ ፈጽሜ ሰው ባያየኝ የር ያየኛል። ለጥፋቴ ቅጣት ከማይታየው ግን ከሚያየው የር (ፈጣሪ)ይደርስብኛል" ብሎ ያምናል። ስለዚህ ቀጻ የሆኑ ተግባራትን በስህተትም ሆነ ሆን ብሎ የፈጸመ ከቀጻ ለመንጻት በባህሉ የተደነገጉ የተለያዩ ከቀጻ የመንጻት ክዋኔዎችን መተግበር የግድ ነው። በጻራ ብሄረሰብ ሴትም ሆነች ወንድ ቀጻ የሚባሉ ተግባራት ተለይተው ይታወቃሉ። ለምሳሌ ባል ሚስቱን ለሰላምታ እንኳን ቢሆን መሳም፣ እጅለእጅ መያያዝ፣ ሽንት ቤት አብሮ መሄድ መአድ አብሮ በአንድ ገበታ መቅረብ ቀጻ ነው። እነዚህን የመሳሰሉ ዋና ዋና የጻራ ብሄረሰብከሥርዓተ ጾታ ጋር የተያያዘ የቀጻ እሳቤ ማሳያዎችን ቀጥሎ እንመለከታለን።

'ሚስት በባሏ መኝታ መተኛት ቀጻ(ነውር) ነው"  ሴት በወንድ፣ ወንድም በሴት ማረፊያ ወይም መቀመጫ ቦታ መቀመጥና መኝታ ላይ መተኛት ቀጻ ነው።ይህ ክልከላ ከወንዶቹ ይልቅ ሴቶቹ ላይ ቀጻነቱ ያመዝናል። ኪቻ ማየት የጀመረች ልጃገረድም ትሁን

ያገባች ሴት ባሏም ቢሆን በወንድ መቀመጫ ላይ መቀመጥ፣መኝታው ላይ መተኛት ቀጻ ነው።ባልና ሚስት መኝታቸውም ሆነመቀመጫቸው ለየብቻ ሲሆንከምሰሶባላይ እና በታች ተብሎ ይለያል። እንግዳም ሲመጣ ወንድ በወንድ፣ሴት በሴት ቦታ ይስተናገዳሉ።ልጆችም ከህጻንነት የእድሜ ክልል ሲያልፉ ሴቶች ወደ እናታቸው ወንዶች ወደ አባታቸው ወይም እደጅ ወጥተው ይቀመጣሉ። ያድራሉ። ባልና ሚስትከ"ባርኮምቴ"(የሙሽርነት ጊዜ) ጀምሮ አብሮ መብላትም ሆነመተኛት ያበቃል።የወንዱ መተኛ ተፍቆ ያማረ ቁርበት ሲሆን የሴቷ መኝታ አሮጌ ቁርበት በአብዛኛው የጠወለገ የእንሰት ቅጠል ነው። የእንሰት ቅጠሉ ሲደርቅ እየጣለች በአዲስ ተቀይረዋለች።አንዲት ሴት የባሏ መኝታ ላይ ብትተኛ ባሏ ዳግም እዚያ መኝታ ላይ አይተኛም።ይህን በተመለከተ አንዲት መረጃ አቀባይ ካለችው ተከታዩ ይገኝበታ፡-

> በጻራ ባህል የወንዱ መተኛ ቁርበት ላይ ሴት አትተኛም። ባሌ ሲፈልግ እኔ የተኛሁበት ይመጣል እንጂ እኔ ወደ ባሌ መኝታ አልሄድም ቀጻ ነው። ባል የሚተኛበት ቁርበት የቦርዴ እንኩሮ ማዘጋጃ በመሆኑ ሴት ብትተኛበት ይረክሳል። እዚያች ሴት ቤትም ሰው ቦርዴ መጠጣት፣ ምግብ መመገብ ይጸየፋል። ቁርበቱ በቃ የወንድ ብቻ ነው። ሴት ልትቀመጥበትም ሆነ ልትተኛበት አይገባም። በስህተትም ሆነ ሆን ብላ አንዲት ሴት የባሏ መቀመጫ ቦታ (መደብ) ላይ ብትቀመጥ አፍርሳ እንደገና ትሰራዋለች፤ መኝታው ላይ ከተኛች ደግሞ አዲስ ቁርበት ይቀይራል።[11]

በተመሳሳይ ሁኔታ ወንድና ሴት ሽንት ቤትአብሮ መሄድና መተያየት ቀጻነት ያለው ተግባር ነው።ሴትሽንት ቤት ስትቀመጥ ወይም ተቀምጣ ከጀርባዋም ሆነከጎንበሆው አቅጣጫ ወንድ በተለይ ባሏ ማየት ላየውም ለታየችውም ቀጻነው። ስለዚህ ይህ ቀጻ መንጻት አለበት። ሚስቱ ያልሆችን ሴት ከሆነ ያየው ወዲያው አንባሯን እንድታሳየው በመጠየቅ ስታሳየው እዚያ ላይ እንትፍ እንትፍ ይላል። ይህ ማለት ከቀጻው ነጻ ማለት ነው።ባል ሚስቱን ሽንት ቤት ካያት፣ ከዚያ ሰአት ጀምሮ እሷ ያዘጋጀችውን አይበላም። አይጠጣም። ስታቀርብም አታቅርቢ አይላትም፤ ለምን እንደማይበላና እንደማይጠጣ ለጓደኛዋ ወይም ለቅርብ ሴት እንጂ ለራሷ አይነግራትም። ይህንን የሰማች ሚስት "ቶሎ ካልነጻን ባሌ ሊሞት ይችላል" ብላ ስለምታምን ከቤቷ ትወጣለች። ቤተሰቧ ወይም የቅርብ የምትለው ጎረቤት ዘንድ ሆና "ቢርሰሳ"[12] መጥቶ እስከሚያነጻ ጊዜያዊ መፍትሄ ታደርጋለች።መፍትሄው በእጇ ላይ ያለ አንባር ወይም ጨሌ ነው።የእጇን አንባርአውልቃ ባሏንበጥርሱ ማስነከስ እናየተነከሰውን አንባር በቤቷየውስጥ ግርግዳ ላይ መስቀል አንዱ ነው። ወይም አንገቷ ላይ ከምታደርገው የጨሌ ዘለላዎች መካከል ጥቁር ቀለም ያለውን ጨሌ (ጃላ ይባላል) አራት ፍሬ አውጥታ በሌላ ክር ላይ አስገብታ ለባሏመስጠት። እሱምበመኖሪያ ቤታቸው የውጭ ግርግዳ ላይ ይሰቅለዋል። ከዚያም ለኤቀትሳው "እስከሚነጻ ቤቴን ሰላም አድርግልኝ" ብላ ሁለት ብር ትሰጣለች። በዚህ መልክ ይቆያሉ።

---

[11] ቃለ-መጠይቅ፣ አቶ ኢርታንቆ ለገሰ፣ 3/8/2011ዓ.ም.።

[12]በትውፊታዊ እምነት የማፈቀዱ ግባራትን የፈጸሙ ግለሰቦችን ለማንጻት ስልጣን የተሰጠው ግለሰብ በጎሳው ስም ቢርሰሳ ተብሎ ይጠራል።

የማንጻት ስርአቱን ለመፈጸም ስልጣን የተሰጠውን "የቢርተትሳ" ጎሳ፣ "ቢርሰሳ" የተባለ የማእረግ ስም ያለውን ተወካይ ግለሰብ ባል በፍጥነት አፈላልጎ የማንጻት ስርአቱ ይከወናል፡፡ ስርአቱን የሚፈጽመውን ግለሰብ ፈልጎ ማምጣት፣ የምትነጻበትን የታቆረና መልኩን ለውጦ የሻገተ ውሃ መፈለግ፣ ማምጣት የባል ግዴታ ነው፡፡ ይህ ውሃ "ሲሀ"(አንድ ቦታ ረግቶ የቆየ ለማለት) ይባላል፡፡ ቢርሰሳ በማለዳ በምትነጻው ሴት ቤት በመገኘት "ሲሀ"ን በቤቱ ውስጥና ውጭ በመርጨት ያነፃቸዋል፡፡ ከዚያ ቡና ተፈልቶ ይጠጣል፡፡ ባል ላነጻው ግለሰብ ከቻለ ከብት ካልቻለ ገንዘብ በስጦታ ይሰጣል፤ ምንም የሌለው ከሆነ ቦርዴ ይጋብዛል፡፡ በዚህ ክዋኔ የተሰራው ስህተት እንዳልተሰራ ይቆጠራል፡፡ በዚህ መልኩ ካልነጻ ግን ሰውዬው ይሞታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ እና በሌሎችም ርእሰ ጉዳዮች መረጃ አቀባይ ከነበሩት ግለሰብ ጋር በተያያዘ የሚያውቁትን የቤተሰብ ታሪክ ከተረኩት መካከል ለማሳያ ተከታዩ ቀርቧል፡-

> የአባቴ ታላቅ ወንድም ሚስቱን ሽንት ቤት አይቷት፣ ለልጆቼ እናት 'ምን ብዬ እነግራታለሁ!'በማለት ዝም ብሎ ያዘጋጀችውን ምግብ በላ፡፡ በልቶም ልጁን ለመዳር ጥሎሽ ለመስጠት ቀጠሮ ስለነበረው ከሚድረው ልጁ ጋር ወደ ጉዳያቸው ሄዱ፡፡ በመንገድ ሳሉ ሁለቱም በሰው እጅ ተገደሉ፡፡ ለሞቱ ምክንያቱን ኤቀትሳ ሲጠየቅሚስቱን ሽንት ቤት ተቀምጣ አይቶ ዝም በማለቱ እንደሆነ ተናገረ፡፡ ኤቀትሳን የጠየቀችው የሟቹ ሚስት ነበረች፡፡ ሲናገርም 'በአንቺ ምክንያት ሞተ' ሲል ዝርዝሩን ጭምር ነገራት፡፡[13]

እነዚህን የመሳሰሉ የሰዎች በድንገትም ይሁን በህመም ምክንያት መሞት ቀጻን መተላለፍ ብቻ ሳይሆን የእምነት ጣጣም ይሆናሉ፡፡ ይህን ፍራቻ ማንም ሰው ቀጻ የሆነን ላለማድረግ ይጠነቀቃል፡፡ ተሳስቶም ከተላለፈ ተናግሮ አንጹኝ ብሎ ይጠይቃል፡፡ሴት ስትሆን ደግሞ በማየቷ ብቻ ሳይሆን ያለ ፈቃድዋ ታይታም ቢሆን ጦሱ ስለሚደርሳት የማንጻት ክዋኔው አካል ትሆናለች፡፡

ቀጥሎ የሚቀርበው ቀጻ ደግሞ ከዝሙትመፈጸምጋር የተገናኘ ነው፡፡ ባልከሚስቱወይምከሚስቶቹ፤ሚስትከባሏውጭ፤ ሁለት ተጋቢዎች ከመጋባታቸው በፊት እንዲሁም ባል ናሚስት ሰው በሚያይበት ቦታ የግብረስጋ ግንኙነት መፈጸም ቀጻ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን የተላለፉ ጥፋታቸውን አምነው ከቀጻ መንጻት አለባቸው፡፡ አንዲት ሴት ተገዳ ተደፍራ ከሆነከቻለች በተደፈረችበት ቦታ ላይ ሆና ከረዘመ በዚያኑ እለት ወደቤቷ ሳትገባ ሌላ ሰው እንዲያውቀው ማድረግ አለባት፡፡አለዚያ ወዳ እንደ ፈጸመች ስለሚቆጠር ቀጻ ነው፡፡ ወንዱ ግን አስግዳጅ እንጂ ተገዳጅ አይሆንም ተብሎ ስለሚታመን አስገድዶ ስለመድፈሩ ተናግሮ መንጻትና ማንጻት ይጠበቅበታል፡፡ ነውሩም በሽማግሌ አደራዳሪነት በከብት ደም በመታጠብና መስቀለኛ መንገድ ላይ በመገረፍ ይነጻል፡፡ የማንጻት እንዲሁም የሁለቱ ቤተሰብ እርቅ የሚፈጸመው በዚሁ እለት ሲሆን ወጪውን በሙሉ የሚሸፍነው ወንዱ ነው፡፡

[13] ቃለመጠይቅ፣ አቶ አካሉ እልኩ ህዳር18/3/2010 ዓ.ም.፡፡

የእርቅ ስርአቱ ሲፈጸም አንድ በሬ ይታረዳል።በበሬው ደም ሽማግሌዎች ባሉበት መስቀለኛ መንገድ ላይ ደፋሪውና የተደፈረችው ሴት፣ሽማግሌዎች ባሉበት የሚያነጻው "ቢርሰሳ" ሥርዓቱን ይመራል። ቢርሰሳ የታረደውን ከብት ደም በውሃ በማቅጠን ያጥባቸዋል። ሌሎች ክዋኔዎችም ከተፈጸሙ በኂላ ባለትዳር ሴት ከሆነች ለባሏ አንዲት ላም በስጦታ ደፋሪው ሰጥቶ የተሰጠቻትን ላም ይዛ ወደ ቤቷ ትመለሳለች።የተደፈረችው ልጃገረድ ከነበረች ማግባት ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ስለሆነ ከተገፈች በኂላ ከታረደው ከብት አንዱን የኂላ እግር(ስጋውን ጭምር) ተሸክማ ወደ ደፋሪው ቤት ትሄዳለች።ያገባም ከሆነ ሁለተኛ ሚስት ትሆናለች።

ለሙት መንፈስ ከሚቀርብመታሰቢያ ጋር የተያያዘ ቀጻም አለ።የወንድ እና የሴት የሙት መታሰቢያቸው የተለያየ ነው። ለወንድ መታሰቢያ ለሙት መንፈሱ ካሻ(መስዋእት) አቅራቢ የተመረጠ ከዘር ሲተላለፍ የመጣ ስልጣን ያለው ግለሰብ(ካሽትሳ) እንዲሁም ቋሚ መስዋእት ማቅረቢያ ቁስ እና ቦታ አለ።የካሻ ጤፍ ያገባች፣ የወለደች፣በጥቅሉ የወር አበባ ያየች ሴት አትፈጭም ገንፎውን አታገነፋም። ገንፎውን ካሽትሳ ያገነፋል ወይም የወር አበባ ያላየች ልጃገረድ ታገነፋለች። ምክንያቱም መስዋእት በወንድ እንጂ በሴት አይቀርብም።

ለሴት ካሻ ሳይሆን እንሰት ይተከላል። ለአያት ወይም እናት የመጀመሪያው ወንድ ልጇ በራሱ ደጃፍ "ኢነኡታ"(እንሰት)[14] ይተክላል። ኡታ እንሰት፣ ሲሆን ኢ እናቴ ማለት ነው። ሌሎች ልጆች ካሉመስዋእቱን ለሚያቀርበው ልጅ አስፈላጊ የሆነውን መዋጮ ሊያዋጡ ይችላሉ። ልጅ ሳትወልድ ለሞተች ሚስት ይኖሩበት በነበረው ቤት ጓሮ ባሏ እንሰት ይተክላል[15]። ለሴት የሚቀርበው የሙት መንፈስ መስዋእት ምልክት ሲታይ እንጂ ቋሚ አይደለም። ከምልክቶቹ ለምሳሌ ከሚቿ የልጅ ልጆች መካከል አንዱ ወይም አንዷ ጥርስ ሲያፋጩ፣ በእንቅልፍ ልብ መጮህ ወይም ቅዠት፣ ተደጋጋሚ ህመም ይገኙበታል። የልጁን የህመም ምክንያት ኤቀትሳ ሲጠየቅ "እናትህ እንሰት ተክልህ፣ ገንፎ እንድታበላት ፈልጋ ልጁን ወይም ልጅቷን ይዛለች" ብሎ መተርጎም የተለመደ እና የታወቀ ነው። የልጁም አባት ቀድሞ ካልተከለ በእናቱ ስም ሁለት እንሰት ይተክላል። በዚህ እንሰት ስር መስዋእቱን በሚስቱ አዘጋጅነት ለኤቀትሳ አስባርኮ ያቀርባል[16]።

[14]ለእናት መታሰቢያ የተተከለ እንሰት ካረጀ ተፍቆ ለምግብነት ይውልና በምትኩ ሌላ እንሰት ይተከላል።

[15]ካገባ፣አዲስ የተገባችው ለመጀመሪያ ሚስቱ መንፈስ የሚቀርብ ቦርዴ እና ገንፎ የሚሆነውን ጤፍ ፈጭታ ታዘጋጃለች።

[16] "እህሉን በዚህ ቀን ፈጭተሽ ለእኔ ስጭኝ" ብሎ ለሚስቱ ይሰጣል። እሷም ቦርዴ አዘጋጅታ ጤፉን ፈጭታ ዱቄቱን ለባሏ ትሰጣለች። ባልም ከቦርዴው ላይ መጀመሪያ ለኤቀትሳ መስጠት አለበት። ኤቀትሳ ሳይቀምስ መጀመሪያ ለእናቱ መንፈስ ከሰጠ የታመመ ልጁ ሊሞት ይችላል ተብሎ ይታመናል። የጤፉን ዱቄት ገንፎ አገንፍቶ መጀመሪያ እራሱ ቀምሶ "እናቴ ቤት ውስጥ ያለውን በሽታ አውጪ፤ ቤቱን ሰላም አድርጊ ቤቴን እርጥብ አድርጊ እኔ ቀምሼያለሁ። በልቻለሁ። አንቺም ብዪ" ብሎ ለእሷ ብሎ በተከለው እንሰት ስር ጉርጓድ በመቆፈር ቦርዴውንም ሆነ ገንፎውን በእንሰት ቅጠል ያስቀምጣል።

በአይነት ከሌሎቹ እንስት የተለየ አይደለም።የሚለየው የሚተከልበት ቦታ በጓሮ በኩል ለመኖሪያ ቤቱ ቅርብ ቦታ በስተግራ መሆኑነው። በግራ የሆነበት ምክንያት እናት ግራ ነች፤ መውለድ እንጂ ዘር (በእሷ ስም የሚጠራ)የላትም። ቀኝ የቤት ምሰሶ ማለት ሲሆን ይህም ወንድ ወይም አባት ነው። ለወንድ መስዋእት የሚዘጋጅምግብ የሚታረድ ከብት ስጋ ሴቶች አይቀምሱም። ሴት እንሰሳ ለአምልኮ ለስእለት አይሆንም።

እስካሁን የቀረበው ትንተናማህበረ-ባህላዊ እና ትውፊታዊ እምነትን መሰረት ያደረገውን የሥርዓተ ጾታ ስሪት ነው። ጽንሰ ሐሳቡ ማህበረሰቡ ለሴትነት የሚሰጠውን ትርጉም፣ ትርጉሙን ለማጉላት የሚጠቀምበትን ምስል፣ ለሴትነት የሚሰጠውን ማኅበራዊ ሚና እና/ወይም የተግባር ወይም የሥራ ድርሻ፣ በእምነት ውስጥ ያለውን እሳቤ እንዲሁም ማኅበራዊ ደረጃ በዋናነት የተመለከተ ነው። ሥርዓተጾታ እና ማህበራዊ ሚና፣ ሥርዓተ ጾታ እና ሀገረሰባዊ እምነት እንዲሁም ነውር እና የሥርዓተጾታ እሳቤ በሚል ጠቅለል ባሉ ርእሶች ስር የቀረበው ነው።

## 3. *መደምደሚያ*

የጥናቱ አጠቃላይ አላማ የጻራ ማህበረሰብ የሥርዓተ ጾታን ምንነት በመመርመር ማኅበረሰቡ ለሴቶች ያለውን አመለካከትና በጥቅሉ ለሴትነት ያለውን አስተሳሰብ ማሳየት ነው። እነዚህም አንደኛ የሴቶችን ማህበራዊ ሚና እና የስራ ድርሻ የሚመለከት ነው። ሁለተኛ ሴቶች በሀገረሰባዊ እምነት ውስጥ ያላቸውን ቦታ የሚመረምር ሲሆን ሶስተኛው በሴቶች ቢታሰቡ፣ ቢደረጉ ነውር የሚባሉትን ልማዶች የሚዘረዝር ነው። ስለሆነም ጥናቱ ከእነዚህ ሶስት ዝርዝር አላማዎች መነሻነት ሶስት ግኝቶችን(finding) ይፋ አድርጓል።

የመጀመሪያው ግኝት የመጀመሪያውን ዝርዝር አላማ መነሻ ያደረገ ሲሆን ይህም ሥርዓተ ጾታ ከማህበራዊ ሚና ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል። ልጆች ይህንን ማህበራዊ ሚና የሚያሳይ ሴት መሆንን፣ ከእናታቸው ስር ስር በመሄድ የምታደርገውን እያደረጉ ይለማመዳሉ። ከፍ ሲሉም አባታቸው የነካውን ባለመንካት መኝታውም ሆነ ማረፊያው ላይ ባለመቀመጥ ገበታ ከእናታቸው ጋር ብቻ በመቅረብ ይለማመዱታል። እናቷ የምትሰራውን በመስራት፣ የምትበላውን በመብላት፣ የማትበላውን በመጸየፍ የቤት ውስጥ የየእለት ተግባርን ትለማመዳለች። ይህን ካላደረገች ግን እንደ እናቷ ሚስት ብሎም እናት ለመሆን ማለፍ ያለባትን የሴትነት ወግ ባለማሟላቷ ባል ማግኘት ብሎም እናት ለመሆን ያዳግታታል። ከዚህም ባለፈ በቤተሰቡ በእናት አባቷ ዘንድ ከፍ ሲልም ከእምነት መሪዎች አካሄዷ ትክክል አለመሆኑን በተለያየ ስልት ይጠቁሟታል። ወንድ ልጅም ህጻንነቱ አልፎ ከእናቱ የቅርብ ክትትል አልፎ እድሜው አስር አመት ገደማ ሲሆን ገበታ ሲቀርብ ከአባቱ ጋር አሊያም በአባቱ ወንበር ተቀምጦ ይሆናል። አዳሩም የወደፊት ጀግንነትን ውጭ ውጭ ማለትን እንዲደፍር ከቤት ወጥቶ ውጭ ቆጥ ሰርቶ በማደር ይለማመደዋል። ሀብት ማፍራትንም በአባቱ እግር እየሄደ እኩዮቹን እያማከረይተገብረዋል፤

ምክንያቱም ሚስት ለማግባት ለጥሎሽ የሚሆን ሀብት ያስፈልጋል። ያለጥሎሽ ሚስት ለማግባት መክጀል ከእሱ አልፎ መዘዙ ለዘመድ አዝማድ ይተርፋልና ነው። አባት ሚናው የቤቱ ዋርካ መሆን እናት ወርካውን ማጠንከር እንጂ በዋርካው መወሰን አትችልም። ምግብ እና የአመጋገብ ልማድ ሌላው የሥርዓተ ጾታ ማሳያ ነው። አሳ እና መሰል በጥቅል በባህር ውስጥ የሚኖርን ፍጡር መብላት ለሴትም ለወንድም ማህበራዊ ደንቡ አይፈቅድም። ሴቶች ደግሞ የአእዋፍት ዝርያን ዶሮና እንቁላልን ጨምሮ አይበሉም። የአመጋገብ ልምዱም ወንድ ከወንድ ሴትም ከሴት ጋር ገበታ ይቀርባል።

ሁለተኛው ዝርዝር አላማ የሀገረሰባዊ እምነትንየሥርዓተ ጾታ የመገለጫ መልኮች የሚመረምር ነው። ግኝቶቹ ሰፋ ያሉና ሀገረሰባዊ እምነት ለሥርዓተጾታ ስሪት መሠረት እንደሆነ የሚጠቁሙ ናቸው።ከሀገረሰባዊ እምነት ውጤት ከሆነው ደንብ አንዱ የወር አበባ እና በብልቷ አካባቢ.ዶላ (እባጭ)የወጣባት ሴት ከማህበራዊ ህይወት ክዋኔዎች እና ከመኖሪያ ቤቷ ወጥታ በተወሰነላት ቦታ ብቻ ታቅባ ትቆያለች። ሌላው ተፈጥሯዊ የሆነው መካንነት ለሴት ብቻ የተሰጠ እንደሆነ ይታመናል። መካንነቱም መጥፎ መንፈስ በመሆኑ ከዚያች መካን ከተባለች ሴት ጋር ይኖራል።ለሴቶች ክልክል የሆኑ የሀገረሰባዊ እምነት መመሪያዎች አንዱመስዋእት አቅራቢ ወንድ መሆኑ ነው። ለመስዋእት የሚሆን ከብት ጾታው ወንድ ነው። እምነታዊ ደንቦችን ለተላለፈ ጥፋት መደምሰሻ የማንጻት ሥርዓት በወንዶች ብቻ ይከወናል። ሴቶች ለጥፋታቸው ቅዱስ መንፈሱን ይቅርታ መጠየቅ እንጂ ይቅር እንዲል መጠየቅ ወይም ይቅር ማለቱን ማወቅ፣ ማረጋገጥ፣ የሚገባውን ግብር ማቅረብ የወንዱ ነው።

ሶስተኛው ግኝትየነውር(ቀጻ) እሳቤዎች የሚገለጡበትን የሥርዓተ ጾታ ማሳያየሚዘረዝር ነው። ነውር እንደጻራ ማህበረሰብ ጾታ ሳይለይ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ እንደየ ተዋረዱ በቤተሰብ በባልና ሚስትመካከል በእምነት መሪ እና በምእመኑ መካከል በግልጽ የሚታወቁ ናቸው። ሚስት በባሏ መኝታ መተኛት በደምሳሳው የወር አበባ ያየች በወንድ መቀመጫ መኝታ መድረስ መንካት፣ መቀመጥ ወይም መተኛት፤በወንበሩ መቀመጥ፣ በአንድ ማእድ መቅረብ ነውር ነው። ከምሰሶ በላይ ለሴት የተከለከለ እና ለወንድ ብቻ የተፈቀደ ነው። ሴት ከምሰሶ በታች ምድጃው ባለበት መመገብያዋ፣ መዋያዋ ማደሪያዋ ነው። ሴት ደጅ ስትወጣ ሽንት ቤት ስትቀመጥ በቤቷም ሆነ እንግድነት በሄዱበት ባሏ እንዳያያት መጠንቀቅ አለባት። ሳትጠነቀቅ ቀርታ ቢያያት ነውር ነው። ሊጋቡ ያሰቡ ጥንዶች፣ ባልና ሚስት ሰው በሚያይበት ቦታ ወይም በባል መኝታ ላይ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ነውር ነው።

በጥቅሉ የዚህ ጥናት ግኝቶችም የሚያሳዩት በሴቶች እና በወንዶች መካከል ያለውን ግንኙነት፣ ማህበረሰቡ በባህሉ፣ አንዱ ማህበራዊ ሚናን የሚመለከት ነው። የባልና ሚስት ድርሻ በቤት ውስጥ የሚንቀሳቀሱበትን ቦታ ጭምር ገድቦ የሚያሳይ ነው። ወንድ ወደ አደባባይ ሴት በማጀት ዙሪያ የሚሳተፉበት የስራ ክፍፍል አላቸው።

በቤተሰቡ በተለይም በልጆች ላይ ያለው የባልና ሚስት ሚናም የእነሱን ፈለግ እንዲከተሉ ማድረጊያ ስልቶች በግልጽ የሚታወቁ በየእለቱ የሚተገበሩ በተግባር የሚኖሩ ናቸው:: ሌላው ከቤት ውጭ በሚሰሩት በማህበረሰብ ውስጥ ሴትና ወንድ ተብሎ የስራ ድርሻና ሚና ቢኖርም በባለቤትነት የሚመራው የሚቆጣጠረው ወንዱ ነው::

በጻራ ማህበረሰብ ሥርዓተ ጾታ የባህሉ፣ የሀገረሰባዊ እምነቱ በጥቅሉ የማህበራዊ ስሪቱ ማሳያ ነው:: ባህል እና እምነቱ ሥርዓተ ጾታን (የሴቶችን እና የወንዶችን) ሚና ፈጥሯል፣ የፈጠረውንም ያጸናባቸው እና ያቆየበት ከባህሉ እና እምነቱ የቀዳቸውን  ስልቶች ተከትሎ ነው:: ይህም ሲባል ሴቶች ይህን ማድረግ ወይም አለማድረግ አለባቸው የሚለውን የሥርዓተ ጾታ ደንቦችን ያቆየው ባይደረግስ ምን ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ በተግባር የሚታይ ምላሽ በመስጠት ነው:: ስርዓቱን ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ደንቡን ለተላለፉት ንሰሀ ወይም ቅጣት በመጣል ቅጣቱን በመተግበር፣ በማስተግበር ነው:: ቅጣቱ በቃል ሊደርስ ይችላል በሚል ባዶ ንግግር ላይ ብቻ የቆመ ሳይሆን ለአብነት የሚሆኑ የደንብ መተላለፍ ቅጣቶችን በሚያውቁት የማህበረሰቡ አካል በሆነ ሰው እና ሁነት የሚገለጥ ነው:: ሴቶች ከተፈቀደላቸው ውጭ ቢያደርጉ ሀገረሰባዊ እምነቱ በራሳቸው በልጆቻቸው በባላቸው በጥቅሉ የእኔ በሚሉት ሰው ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል የሚል የጸና እምነትን ተክሏል:: ይህም የባህሉ እና የእምነቱ አስቀጣይ እና ተካይ ማህበረሰቡ ብቻ ሳይሆን ግለሰቡ ጭምር መሆኑን ማሳያ ነው:: ስለዚህ ከሚያደርጉት ይልቅ የሚደርሰውን ጉዳት ፍራቻ እነሱም አያደርጉም ልጆቻቸውም የሚደረግ እና የማይደረገውን ባህልም ሆነ እምነት እየተማሩ እያወቁ እንዲያድጉ ያደርጋሉ:: ባህሉን በተግባር ኖረው በማለማመድ ለትውልድ ማሸጋገራቸው የሥርዓተጾታ ደንቡ መሰረቱ የጸና እንዲሆን አድርጎታል:: ማህበረሰቡ ደንቡን ለሚያከብሩት ይሸልማል፤ ሽልማቱም ለምሳሌ ለሴትነት የተቀመጡ ልማዶችን ያከበረች ሴት መልካም እናት ጥሩ ሚስት ጎበዝ ልጃገረድ ተብላ ለሌላው አርአያ ትሆናለች::

## ማጣቀሻ ጽሑፎች

ለማ ንጋቱ:: 1999:: በየም ብሄረሰብ ጾታ ተኮር ተረቶች የወንድ እና ሴት ምስል ትንተና::ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)::

አራጌ ይመር::2001::"በአራት ገድሎች ላይ የተደረገ ዐውደ ንባባዊ ትንታኔ::" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለትምህርት፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)::

አዲሱ ዘገየ:: 2000::"እንስታዊ የሥነ ጽሑፍ ሂስ ከ1984-1997ዓ.ም. በታተሙ የሴቶች የግጥም መጻህፍት ውስጥ::" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)::

አዳነች ካሳ:: 2002:: *የሀድያ ሴቶች በቡድን የሚከውኗቸው ተግባራት ላይ የተመሠረተ ቁሳዊባህል ጥናት::* *ሥነጽሁፍና ፎክሎር* ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ (*ያልታተመ*)::

ኤልሳቤጥ *መንግስቱ*:: 2005:: *የሶዶ ጉራጌ እና የሴቶች ስርዓተ ጾታዊ ሚና እና ማህበራዊ ደረጃዎች::ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ* የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ *ሥነጽሁፍናፎክሎርክፍለትምህርት*፣ አዲስ አበባ (*ያልታተመ*)::

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ *መንግስት*:: 2001:: በብሄረሰቦች ምክር ቤት በባህል *ታሪክና* ቅርስ ጥናት ተቋም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ፕሮፋይል:: *ሃዋሳ*:: ፍቅረሰላም ማተሚያ ቤት::

የሺ ዋስ አለሙ:: 2007:: *መልከአ ሴትነት እና ሀይለ ሴትነት*፤ በደርሶ *መልስ*፣ *ራማቶሀራ፣ዴርቶጋዳ እና ግርዶሽ እንስታዊ ንባብ*፣ *ሥነጽሁፍና* ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ አዲስአበባ (*ያልታተመ*)::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህል አካዳሚ:: 2006:: *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*::አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፕሬስ::

ፍሬህይወት ባዩ*::* 2013:: *የጻራ ብሄረሰብ ትውፊታዊ እምነት::* ዜና ልሳን፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዴሚ *መጽሄት* ቅጽ 28፣ቁጥር 2:: *ገጽ* 24-46::

Addisalem Melesse and Abera Mekuria. 2013. Ethino History of the Chara people. Southern Nations Nationality and Peoples Regional State, Bureau of Culture and Tourism.

African Center for Women.1997.Traditional and Cultural Practices Harmful to the Girl Child. A cross Sectional Review, Economic Commission for Africa [Addis Ababa].

Alem Desta. 2007. The Candaes. Addis Ababa: Ethiopian Millennium Foundation.

Amdeberhan Gizaw. 2007. Gender Equality Status of Ethiopian in the Global Context. Reflections, 15, 47-49 Addis Ababa: Heinrich Boll foundation.

Fiorenza, Elisabet. 1986. *A Feminist Theological Reconstruction of Christian Origins*. London: Sims press.

Hirut Terefe. 2002. Violence Against Women from Gender and Cultural Perspective. Reflections, Panos Ethiopia, No 7, 1-12, Addis Ababa.

Jejaw Ambie. 2011. "The Myth of Ideal Masculinity: Traits, Blood Revenge Practicesand Their Impact on Women in Sebentera Kebele*,* Dabat Woreda, North Gonder Administrative Zone." A thesis Submitted to School of Graduate Studies (Unpublished).

Jemila Adem. 2014. "Women and Indigenious Conflict ResolutionInstitutions inOromia: Experience from Siinqee of the Wayyu Shanan Arsi Oromo in Adami Tullu Jiddu Kombolcha District of the ONS." A thesis Submitted to School of Graduate Studies(Unpublished).

Kalkidan Bekele. 2007. "Cultural Practices that affected the status of womenin Benishangul Gumuz, Mandera Wereda." A thesis Submitted to the Institute of Gender Studies (Unpublished).

Lange, Werner. 1975. Gimira (Remnants of a vanishing Culture), Inaugural zur ErlangungdesGradeseines Doktors der philosophie im Fachbereich FachbereichGechichtsitat Zu Frankfurt/Main.Vorglegt.von.

Fiona, Leach. 2004. Practising Gender Analysis in Education, Oxford, UK. Oxfam, Information Press.

Selamawit Mecca. 2006. "Hagiographies of Ethiopian Female Saints with Special Referenceto Gadla Krestos Samra and Gadla Feqrta Krestos." Journal of African Cultural Studies.Vol. 18, (2). London: Rutledge.

Tsion Yohannes. 2007. "Gender issues and women's portrayal in secular Amharic Songs Produced in Cassettes (in 1997 E.C.)" A thesis Submitted to the school of Graduate Studies of AAU (Unpublished).

Yilma Suntan. 2009. "The role of Status of women in the food system of the Konso of Southwest Ethiopia." A thesis in social Anthropology (Unpublished).